# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 256 ግንቦት 16 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ፡-

## - ከጂዲፒ ያለውን የ6 ነጥብ 8 በመቶ ድርሻ ወደ 17 ነጥብ 2 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል

## - የ50 በመቶ የኢንዱስትሪ ምርታማነት ወደ85 በመቶ ለማሳደግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከጂዲፒ ያለውን የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ድርሻ ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የ50 በመቶውን የኢንዱስትሪ ምርታማነት ወደ85 በመቶ ለማሳደግ እንቅስቃሴ መጀመሩ ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በድሬዳዋ ከተማ ባዘጋጀው ስለኢትዮጵያ በተሰኘውና በኢንዱስትሪ ልማት ላይ በመከረው መድረክ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ዘላቂነት እንዲኖረው በማድረግ አምራቹን ዘርፍ ይበልጥ እንዲነቃቃ ለማድረግ ታቅዷል። በንቅናቅውና መሰል ስራዎች የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከጂዲፒ ያለውን የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ድርሻ ለማሳደግ እየተሰራ ነው።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአምራች ዘርፉን ብቻ ሳይሆን የተመጋጋቢ ዘርፎችንም አቅም ከማሳደግ አኳያ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን አቶ መላኩ ጠቁመዋል።

በዚህ ረገድ የተዘጉ ፋብሪካዎች ድጋሚ ስራ እንዲጀምሩ በማድረግ ፣ ምርታማነታቸውን የቀነሱ ኩባንያዎችን ምርታማነት እንዲያድግ በማድረግና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች እንዲመጡ በመርዳት ረገድ እንዲሁም የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ጠቃሚ ልምድ የተገኘበት መሆኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በ2014 በጀት ዓመት ግማሽ በኋላ መጀመሩን ያስታወሱት ሚኒስትሩ፤ እንደነማሌኸያ፣

የኢንዱስትሪውን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ መላኩ አለበል

ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

# ‹‹ዓለም አቀፋዊ ብቃትን የተላበሱ የሠራዊት አመራሮችን ለማፍራት እየሰራን ነው››

## - ብርጋዴር ጄኔራል ቡልቲ ታደሰ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ አዛዥ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የአገርን ደህንነት ለማስጠበቅ በዓለም አፋዊ አካባቢያዊና አገራዊ ስትራቴጂካዊ የደህንነት ጉዳዮች ላይ ብቃት ያላቸው አመራሮችን ለማፍራት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል ቡልቲ ታደሰ ገለጹ፡፡

ብርጋዴር ጄኔራል ቡልቲ ታደሰ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሳሳቢ የሆነውን አገራዊና አለም አቀፋዊ ሁኔታ በመረዳት በመከላከያ አቅም ብቻ መፍታት የማይቻልበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ መቋቋምና መመከት የሚቻለው ሲቪሉ አመራር፣ ማህበረሰቡና ያገባናል የሚሉ የአስተዳደር አካላትን ያቀፈ አካባቢያዊና ስትራቴጂያዊ ትምህርትና ስልጠና የወሰደ ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት አቅዶ እየሰራ ነው፡፡

እንደ አዛዡ ገለጻ፤ አሁን ያለው አገራዊ ስጋት የአንድ ጉዳይ ክስተት ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሚነካ በመሆኑ ኮሌጁ ከደህንነት ተቋማት፣ ከሲቪል አመራር፣ ከወታደራዊ አመራር ከሁሉም ዘርፍ የተውጣጡ ባለድርሻ አካላትን ተቀብሎ በምርምርና በስልጠና በማብቃት የአገርን ደህንነት ለማስጠበቅ ሚናቸውን እንዲወጡ እያደረገ ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ የሚሰጠው የስልጠና ዘርፍ የደህንነት ስትራቴጂ ሲሆን፤ አገራዊ ጥቅሞች ምንድናቸው?፣ የአገር ደህንነት ምንድን ነው?፣

‹‹ዓለም አቀፋዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ













# ‹‹ባለሀብቶች መዋዕለ ነዋያቸውን ድሬዳዋ ላይ ቢያፈሱ ትርፋማ ይሆናሉ››

## - አቶ ከድር ጁሃር የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ባለሀብቶች መዋዕለ ነዋያቸውን ድሬዳዋ ላይ ቢያፈሱ ትርፋማ እንደሚሆኑ የድሬዳዋ

‹‹ባለሀብቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# ክልሉ በወሰደው እርምጃ ከ4 ሺህ 500 በላይ ተጠርጣሪ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ማዋሉን ገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ክልሉ በወሰደው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ እርምጃ ከአራት ሺህ አምስት መቶ በላይ ተጠርጣሪ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ማዋሉን የአማራ ክልል ሰላም እና ጸጥታ ቢሮ ገለጸ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ጣሰው ትናንትና በሰጡት መግለጫ፤ ጠላት ለዳግም ወረራ እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት ከውስጥ እና ከውጭ የጠላትን ተልዕኮ ወስደው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ግለሰቦች መኖራቸውን ጠቁመዋል። በፍርድ ቤት ተፈርዶባቸው በሽብርተኛው ትህነግ ወረራ ወቅት ከማረሚያ ቤት ያመለጡ እና በተለያዩ ሕገወጥ ድርጊቶች የተሳተፉ ተጠርጣሪዎችን መንግሥት በቁጥጥር ሥር ማዋሉን ገልጸዋል።

በተወሰደው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሥራ ከአራት ሺህ አምስት መቶ በላይ ተጠርጣሪ ግለሰቦች በቁጥጥር እንደዋሉም ኃላፊው አስታውቀዋል።

ከዚህ ውስጥ 210 በነፍስ ግድያ ተጠርጥረው ተከሰው የምርመራ ሂደቱ ለሕልውና ዘመቻው ቅድሚያ በመስጠት ሳይታይ የቆየ፤ ከ40 በላይ ተጠርጣሪዎች ደግሞ በፍርድ ቤት ተፈርዶባቸው በሽብርተኛው ትህነግ ወረራ ወቅት እና በተለያዩ ምክንያቶች ከማረሚያ ቤት ያመለጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተጨማሪ 39 ተጠርጣሪዎች በግድያ እና በልዩ ልዩ ወንጀሎች ተከሰው በሌሉበት ተፈርዶባቸው የነበሩ፤ 917ቱ ደግሞ ከውስጥና ከውጭ ተልዕኮ ሲቀበሉ የነበሩ ጸጉረ ልውጦች ሲሆኑ፤ የመጡበት ዓላማ እየተጣራ እንደሚገኝም ኃላፊው አብራርተዋል።

ከ1 ሺህ 780 በላይ ሕዝባዊ ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ፣ በልዩ ልዩ ወንጀል በመሳተፍ ጭምር የተጠረጠሩ፣ በጸጥታ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ አባላትም በቁጥጥር ስር እንደዋሉ ተጠቅሷል።

የክልሉ ሰላም እጦት እንዲባባስ፣ ከክልሉ ውስጥ እና ከክልሉ ውጪ ተልዕኮ ተቀብለው ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሲሠሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎችም መያዛቸውን አስታውቀዋል።

ኃላፊው በመግለጫቸው እንዳነሱት፤ የተለያዩ ወንጀሎችን እየሠሩ በዕውነተኛው ፋኖ ስም የሚነግዱ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ሲውሉ፤ ከእውነተኛ ፋኖ ጋር በማስተሳሰር ሥም የሚያጠለሹ ግለሰቦችና ቡድኖች ተቀባይነት የላቸውም ብለዋል።

ትክክለኛ ለሀገር የቆመውን ፋኖ በማደራጀት እና በማሰልጠን በመንግሥት አደረጃጀት ስር ሆኖ ለክልሉ አንድ አቅም እንዲሆን ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የክልሉን ሕዝብ ሰላም እና ደኅንነት ዋስትና ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። መንግሥት የሚታዩ ሕገወጥ ድርጊቶችን የመከላከል፣ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ እና የሕዝብን ደኅንነት የማስጠበቅ ሚናውን እየተወጣ ነው ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት እየወሰደ ባለው የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ተግባር ሕዝቡ እያሳየ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የተጀመረውን የጦር መሳሪያ ምዝገባ በተመለከተ ኃላፊው በክልሉ ነዋሪው ያለውን የጦር መሳሪያ ሕጋዊ አድርጎ የሀገሩን ሰላም እንዲጠብቅ መንግሥት የጦር መሳሪያ ምዝገባ ፈቅዶ እየሠራ ይገኛል ነው ያሉት።



**አቶ ደሳለኝ ጣሰው**

ምዝገባው እስከ ግንቦት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ እንደሚካሄድም ኃላፊው ገልጸዋል።

ምዝገባው እንደተጠናቀቀም የትጥቅ አያያዝ እና አጠቃቀም ሕግን አስመልክቶ ሥልጠና እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

ኃላፊው የክልሉ መንግሥት እየወሰደ ላለው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሥራ ሕዝቡ እያሳየ ላለው ድጋፍ አመስግነዋል። አሁንም ሕገወጥነትን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ሕዝቡ ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።



# በሣምንቱ ከ10 ሺህ ቶን በላይ ሰብዓዊ ዕርዳታ ወደ ትግራይ ክልል መድረሱ ተገለጸ

አዲስ አበባ፡- በዚህ ሣምንት ከ10 ሺህ ቶን በላይ የምግብ እና የነፍስ አድን አቅርቦቶች ትግራይ ክልል መድረሳቸውን የዓለም የምግብ ፕሮግራም ገለጸ፡፡

የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦቶቹ በታጀቡ 163 የጭነት ተሽከርካሪዎች ሁለት ጊዜ ወደ ትግራይ ክልል መጓጓዛቸውን የዓለም የምግብ ፕሮግራም በመረጃው አመላክቷል፡፡

የዓለም ምግብ ፕሮግራም አጋሮቹን አመስግኖ ከፈረንጆቹ ሐምሌ ወር 2021 ጀምሮ ትግራይ ክልል የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት ጭነው ከደረሱት የጭነት ተሽከርካሪዎች ከ100 በላይ የሚሆኑት አቅርቦቶቹን ወደ ክልሉ አድርሰው መመለሳቸውንም አስታውቋል፡፡

# በሶማሌ ክልል በድርቅ የተፈናቀሉ ነዋሪዎችን መልሶ ለማቋቋም ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል በድርቅ ምክንያት የተፈናቀሉ ነዋሪዎችን መልሶ ለማቋቋም ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሐመድ ገለጹ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ በኢትዮጵያ የጀርመን አምባሳደር እስቴቨን አውር እና በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን ተወካይ ዶክተር ማማዱ ዲያን ከተመራ የልኡካን ቡድን ጋር ተወያይተዋል።

በውይይቱ በክልሉ የተከሰተው ድርቅ በህዝቡ ላይ ስላደረሰው ጉዳት፣አሁን ላይ በክልሉ ስላለው የድርቁ ሁኔታ እንዲሁም ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለህዝቡ የሚያስፈልገውን ድጋፍ ማድረግ ስለሚቻልባቸው ጉዳዮች ምክክር ተደርጓል።

በውይይቱ ላይ የአቶ ሙስጠፌ መሐመድ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ነዋሪዎች ከመኖሪያ አካባቢዎች መፈናቀላቸውን ጠቁመው፤ በተባበሩት መንግሥታትና አለም አቀፍ ሀገራት ድጋፍ ለህዝቡ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖሩ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

የልኡካን ቡድኑ አባላት በቆሎጂ የተፈናቃዮች መጠለያ ማእከል የሚገኙ ተፈናቃዮች ያሉበትን ሁኔታ ይጎበኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ከክልሉ መገናኛ ብዙኃን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።



# “ሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት በሙሉ አቅሙ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም”

- ተገልጋዮች

# “አዳዲስ ሸገር ባሶችን የመግዛት እና በመለዋወጫ እጦት የቆሙ ባሶችን ወደ አገልግሎት በማስገባት አቅርቦቱን የማሳደግ ስራ ይሰራል”

- ሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- የሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት በሙሉ አቅም የመጫን እና ፌርማታ የመዝለል ችግሮች አሉ ሲሉ ተሳፋሪዎች ቅሬታቸውን ገልጸዋል። የሸገር አውቶቡስ አገልግሎት በበኩሉ አዳዲስ ሸገር ባሶችን የመግዛት እና በመለዋወጫ እጦት የቆሙ ባሶችን ወደ አገልግሎት በማስገባት አቅርቦቱን የማሳደግ ስራ ይሰራል ብሏል፡፡

አቶ ሰለሞን አማረ የሸገር አውቶቡስ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ግለሰቡ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ሃሳብ፤ የሸገር ድጋፍ ሰጪ ባሶች ከመጡ በኋላ በትራንስፖርት አገልግሎቱ ላይ የተሻለ አቅርቦት ቢኖርም ከመነሻ በኋላ በሙሉ አቅም የመጫን ችግር ይታያል ብለዋል። እንዲሁም ተሳፋሪን የማመናጨቅ የስነምግባር ችግሮችም ይታያሉ ብለዋል።

ከሜክሲኮ ጀሞ ትራንስፖርት የሚጠቀሙት ወይዘሮ ቤዛዊት ተሾመ በበኩላቸው፤ ሸገር ድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች በሚያቆሙበት ፌርማታ ላይ የመደበኛ ሸገር ባሶች የማይቆሙና ፌርማታ የሚዘሉ መሆኑ ተሳፋሪውን እያማረረ ነው ብለዋል። ከሜክሲኮ ጀሞ አንድ ድረስ አራት ብር የሚከፈለውን ታሪፍ አብዛኛዎቹ ቲኬተሮች አምስት ብር የማስከፈል እና መልስ ለመመለስ ፍቃደኛ ያለመሆን ችግር አለ ብለዋል።

የሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ቢተው ደመላሽ በበኩላቸው፤ በሸገር የትራንስፖርት በኩል ያለውን የፍላጎት እና የአቅርቦት አለመመጣጠን ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ተናግረዋል። የስኩል ባሶች ጠዋትና ማታ ተማሪዎችን አድርሰው ከተመለሱ በኋላም ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጋቸውን አስታውሰዋል።

የሸገር ባስ ትራንስፖርት አቅርቦቱን ለማሻሻል በቀጣይ አዳዲስ ባሶችን ከመግዛት ጀምሮ በመለዋወጫ ምክንያት የቆሙ ባሶችን አስፈላጊው መለዋወጫ ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል። መለዋወጫ ከውጭ የሚገባ መሆኑ እና ወቅታዊ የመለዋወጫ ዋጋ መጨመር ጫና ቢኖረውም በአጭር ጊዜ ችግሩ መፍትሔ እንዲያገኝ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እየተሰራ ነው ብለዋል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተሳፋሪን ማመናጨቅ፣ መስመር መዝለል፣ መሳደብ፣ የአገልጋይነት ስነልቦና ማጣት የመሳሰሉ ችግሮች መኖራቸውን አምነው፤ ችግሩን የሚፈጥሩ ሹፌሮችና ቲኬተሮችን በመከታተል እርምጃ እየተወሰደ መሆኑንም ገልጸዋል።

በ230 መደበኛ ባሶች አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት የመደበኛና የድጋፍ ሰጪ ሸገር ባሶች፣ ከትምህርት ሰዓት ውጪ የስኩል ባሶችንም ጭምር ለብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት እያዋለ መሆኑን ተናግረዋል።

ተቋሙ አጠቃላይ 125 የመደበኛ ሸገር ባስ መስመሮች እንዳሉትና በቅርቡም በቃሊቲ በመሳሰሉት ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎች የመደበኛ ሸገር አገልግሎት የሚጀምር መሆኑን አሳውቀዋል።

የሸገር ባሶች አሰራር በ1000 ሜትር ፌርማታ የሚቆም መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ሆኖ ፌርማታ የሚዘሉ አንዳንድ አሽከርካሪዎች እና በአግባቡ ህብረተሰቡን የማያገለግሉ ቲኬተሮች ላይ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ገልጸዋል።

በከተማዋ የትራንስፖርት ቁጥር እየበዛ መምጣቱን ተከትሎ የምልልስ መጠኑን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደጉን እና እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ከአራት እስከ አምስት የነበረው መደበኛ ምልልስ አሁን 16 ደርሷል:: ሆኖም እራሱን የቻለ የሸገር መደበኛ ባሶች መጫኛና ማውረጃ ቦታ ያለመኖር አገልግሎቱ ላይ እንቅፋት መፍጠሩን ተናግረዋል፡፡

ከነዳጅ ጭማሪ ጋር ተያይዞ መንጠባጠብ ያሳዩ የተወሰኑ ድጋፍ ሰጪ ባሶች አሁን ወደ ስራ እየገቡ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ቀደም ሲል ከከተማዋ የሚጠፉ የሚደበቁ ድጋፍ ሰጪ ባሶች እንደነበሩ እና ከ69 ባሶች በላይ ከስራ የተባረሩ መሆኑን አስታውሰው፤ ተቋሙ በሸገር ድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች ላይ ተግባራዊ ባደረገው በጂፒኤስ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ቁጥጥር የሚደበቁ እና የሚጠፉ ባሶችን የማስቀረት እና ምልልስ የመጨመር ስራ ላይ ውጤት የተገኘ መሆኑንም አመላክተዋል።

የድጋፍ ሰጪ አውቶቡሶች የሶስት ወር ክፍያ ያለመከፈል ቅሬታ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ስራ አስኪያጁ ሲመልሱ፤ ድጋፍ ሰጪ ባሶችን በውል ደረጃ መዋዋልና ክፍያ የማስተባበር ኃላፊነቱ የትራንስፖርት ቢሮ መሆኑን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ እጸገነት አበበ በበኩላቸው፤ ከድጋፍ ሰጪ ሸገር ባስ ባለቤቶች ቅሬታ ሲቀርብበት የነበረው የመጋቢት ወር ክፍያ መከፈሉን ገልጸው፤ እስከ ሚያዚያ 30 ያለው አቴንዳንስ የሰራ ያልሰራ ተጣርቶ የሚከፈል በመሆኑ በሂደት ላይ ነው ብለዋል። በክፍያ አሰራሩም አንድ ድጋፍ ሰጪ አውቶቡስ አንድ ወር ሸገር ብዙኃን ትራንስፖርት መስራቱን በተያዘው አቴንዳንስ ለአዲስ አበባ ትራንሰፖርት ቢሮ ከተላከ በኋላ እንደገና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የሚላክና ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ገልጸዋል።



# ሌተናል ጀኔራል ይልማ መርዳሳ አየር ምድቡ እራሱን እያደራጀና እያዘመነ መሆኑን አስታወቁ

አዲስ አበባ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል “ሠራዊት ሀገር እንጂ ብሄር የለውም” ከሚለው የአስተሳሰብ ለውጥ ጀምሮ በአደረጃጀት በትጥቅና ስልጠና እንዲሁም በሰው ኃይል ግንባታ እራሱን እያደራጀና እያዘመነ እንደሚገኝ የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ ሌተናል ጀኔራል ይልማ መርዳሳ ተናገሩ።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል የማዕከላዊ አየር ምድብ በግዳጅ አፈፃፀማቸው የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የሠራዊቱ አመራርና አባላት የዕውቅናና የማበረታቻ ሽልማት ፕሮግራም አካሂዷል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል ዋና አዛዥና የአድዋ ድል ጀግና ሜዳይ ተሸላሚ ሌተናል ጀኔራል ይልማ መርዳሳ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው እውቅናና ሽልማት እና የሥራ መመሪያ ሰጥተዋል።

ሌተናል ጀኔራል ይልማ መርዳሳ በዚሁ ጊዜ ባደረጉት ንግግር፤ አየር ኃይሉ “ሠራዊት ሀገር እንጂ ብሄር የለውም” ከሚለው የአስተሳሰብ ለውጥ ጀምሮ በአደረጃጀት በትጥቅና ስልጠና እንዲሁም በሰው ኃይል ግንባታ እራሱን እያደራጀና እያዘመነ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በሰሜን ዕዝና ሰሜን አየር ምድብ ላይ የፈፀመውን አረመኔያዊ ጥቃት ተከትሎ በተወሰዱት ተከታታይ ዘመቻዎች የአየር ምድቡ ጀግኖች መስዋዕትነት ጭምር በመክፈል አኩሪ ታሪክ ሰርተዋል ብለዋል ዋና አዛዡ።

“በቀጣይም ለሚጠብቀን ማንኛውም ግዳጅ እራሳችንን ይበልጥ በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ የሚመጥን ታላቅ አየር ኃይል የመገንባት ጉዟችንን አጠናክረን እንቀጥላለን” ሲሉ መናገራቸውን ከመከላከያ ሠራዊት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

የማዕከላዊ አየር ምድብ አዛዥ ኮ/ል ወንዱ ኬዳ በበኩላቸው፤ አየር ምድቡ ከተቋማዊ ሪፎርሙ ወዲህ በስልጠናና በጥገናው ዘርፍ ብሎም ዝግጁነትን በማረጋገጥ ረገድ ስኬቶችን በማስመዝገብ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በአየር ምድቡ የተጀመሩ የለውጥ ስራዎችና ምቹ የስራ ቦታን የመፍጠር ጅምሮችን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

እውቅናና የማበረታቻ ሽልማት ከተሰጣቸው የሠራዊት አባላት በሰጡት አስተያየት፤ዕውቅናና ሽልማቱ የበለጠ የስራ ሞራልና ተነሳሽነት የሚፈጥርላቸው መሆኑን ገልፀው፤ ወደ ፊትም የሚሰጠንን ማንኛውም ግዳጅ ለመወጣት ዝግጁ ነን ብለዋል።

# መንግሥት ሰላም በማስፈን ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተገለጸ

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ:- መንግሥት ሰላም በማስፈን እና ጠንካራ የደህንነት መዋቅር ያለው አገር በመፍጠር ዘላቂና ወጥነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲመዘገብ ምቹ መደላድል መፍጠር ቀዳሚ ተግባሩ ማድረግ እንዳለበት ተገለጸ።

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ዶክተር ጉቱ ቴሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ መንግሥት ሰላም በማስፈን እና ጠንካራ የደህንነት መዋቅር በመፍጠር ዘላቂ እና ወጥነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲመዘገብ ምቹ መደላድል መፍጠር ይኖርበታል።

ዘላቂና ወጥነት ያለው የምጣኔ ሀብት እድገት አለመኖር በሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል የጠቆሙት ዶክተር ጉቱ፤ በአገር ሰላም መስፈን እና የፖለቲካው መረጋጋት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት የማስተካከል አቅም እንዳለው ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ ያልተረጋጋ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ለበርካታ አመታት ግጭት ውስጥ መቆየት፣ በቴክኖሎጂ አለመዘመን፣ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲሁም የዘልማድ አሰራሮች ለሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እድገት ማነቆዎች መሆናቸውንም አብራርተዋል።

የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ሲሻሻል እና ዋና ዋና የኢኮኖሚ ማነቆዎች ሲቀረፉ የምጣኔ ሀብት ዘርፍ እየተስተካከለ እንደሚሄድ፣ መንግሥትም ሙሉ ትኩረቱን የዜጎች እድገት ተኮር ተግባራት ላይ ሊያደርግ እንደሚችል ገልጸዋል።

ለዘመናት በኢትዮጵያ ጠንካራ የኢኮኖሚ ስርዓት አለመዘርጋት ዘርፉ በአብዛኛው በፖለቲካው ጥገኛ ሆኖ በመቆየቱ ነፃ የኢኮኖሚ ስርዓት ለመዘርጋት አዳጋች እንደነበር ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ውስጥ በተለያየ ጊዜ የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮችና አሁንም የቀጠሉ የደህንነት ስጋቶች ለሀገሪቱ



ዶክተር ጉቱ ቴሶ

የምጣኔ ሀብት እድገት ችግሮች መሆናቸው ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ፈተናዎች መሆናቸውንም ነው ዶክተር ጉቱ የተናገሩት።

በየወቅቱ መልካቸውን በመቀያየር የሚከሰቱ አለመረጋጋቶች የመንግሥትና የግል ዘርፉን ሀብት በማውደም፣ የሰዎችን ህይወት በመቅጠፍ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍሰቱ ላይ ጥላሸት በመቀባት የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት አደጋ ውስጥ መክተቱንም ተናግረዋል።

መንግሥታት በተለዋወጡ ቁጥር የቀደመውን የንግድና የኢንቨስትመንት ስርዓቶችን በማስወገድ እንደ አዲስ ቀርጾ ዘርፉን ማዋቀር ወጥ የሆነ የኢኮኖሚ ስርዓት እንዳይገነባ ማድረጉን አስታውሰው፤ ከዜሮ የመጀመር ባህልን በማስወገድ ያለውን የኢኮኖሚ ስርዓትና ልምድ ማስቀጠል፣ የሚታዩ ክፍተቶችንም በማረም እርስ በእርስ እየተገነባ የሚሄድ ስርዓት መገንባት ተገቢ መሆኑንም አንስተዋል።

ከአየር ንብረት ለውጥ መዛባት ጋር ተያይዘው የሚመጡና የኢኮኖሚውን ዘርፍ ሊጎዱ የሚችሉ ሁኔታዎችም እንዳሉ ታሳቢ በማድረግ መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ በመታጠቅ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ረገድ ውስንነት መኖሩን አንስተዋል። ሂደቱም ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚደረገው ሽግግር ተግዳሮት መሆኑን ገልፀዋል።

የግብርና ዘርፉ በባህል፣ በሃይማኖት እንዲሁም በሌሎች ልማዶች ተሸብቦ መቆየቱም ቀጣይነትና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዳይመዘገብ ተጽእኖ ማሳደሩን አንስተዋል።

እንደ ዶክተር ጉቱ ገለፃ፤ የምጣኔ ሀብቱ ተግዳሮቶች በርካታ ቢሆኑም ሌሎች አስቻይ እድሎች አሉ። በኢትዮጵያ ለግብርና እንዲሁም ለኢንቨስትመንት ስራዎች ምቹ የአየር ሁኔታ በመኖሩ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአግባቡ እንዲሳለጥ ማድረግ ተገቢ ነው።

የግብርናውን ዘርፍ በማዘመንም በሁሉም አካባቢዎች ለእርሻ የሚውል መሬትን በአግባቡ በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ምርትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት አሰራር መዘርጋት ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሀብቶቿ የበለጸገች፤ በርካታ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት በመሆኗ ይህንን የተፈጥሮ ሃብት ወደ ገቢ በመቀየር የሀገርን ኢኮኖሚ ማሳደግ እንደሚገባም መክረዋል። አምራች የሰው ሃይል ባለቤት እንደመሆኗም በክህሎት የበቁ ዜጎችን ወደ ውጭ ሀገራት በመላክና በሀገር ውስጥ መጠቀም ቀሪ ተግባራት መሆናቸውን አንስተዋል።

## ‹‹ዓለም አቀፋዊ ብቃትን የተላበሱ የሠራዊት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንዴትስ የአገር ደህንነት ይጠበቃል?፣ የአገርን ደህንነት የሚያስጠብቁ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?፣ የሚሉና መሰል ትምህርቶች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በተጨማሪም የስትራቴጂ አመራር ጥበብና ሀብትን እንዴት በአግባቡ መጠቀምና መምራት እንደሚቻል በትኩረት ስልጠና እተየሰጠ ስለመሆኑ ብርጋዴር ጀኔራሉ ገልጸዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ የአገርን ደህንነት በሚገባ የሚያስጠብቁ ወታደራዊና ሲቪል አመራሮችን ለማፍራት ከመቼውም ጊዜ በላይ በትኩረት እየሰራ ነው ያሉት አዛዡ፤ አሁን በዓለም ላይ ያለው ውስብስብ የሆነ የምድር፣ የአየር፣ የባህርና የመሳሰሉ የጥምር ጦር ዘመቻን እንዴት ማቀድና እንዴት እንደሚመራ ማወቅ የግድ የሚልበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም አቅዶ የሚመራ መሪ፣ አለም አቀፋዊ፣ አካባቢያዊ ሁኔታና የአገር ጥቅም የሚያስከብር አመራር ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ ዋር ኮሌጁ በትኩረት እየሰራ ነው፡፡

እውቀትና የአመራር ጥበብ፣ ሳይኖር ጦርንና አገራዊ ሀብትን መምራት ስለማይቻል የአገርን ደህንነት በተገቢው መንገድ ለመጠበቅ ዋር ኮሌጁ ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፡፡ ከሰሞኑ የተመረቁት ከፍተኛ ወታደራዊ አመራሮች በአገር ህልውና ዘመቻው ላይ ዋናውን የጦር አመራር እየመሩ የነበሩ ናቸው፡፡ የአገርን ጥምቅ ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ወታደራዊ፣ ስትራቴጂያዊ እውቀት ያለው መሪ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ የአገሪቱ ከፍተኛ ወታደራዊ ተቋም ሲሆን፤ የማይገመትና ውስብስ የሆኑ ዓለም አቀፍ የደህንነት ስጋቶችን የመተንተን የመረዳትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በጋራ ተልዕኮን የመወጣት ብቃት ያላቸው ስትራቴጂክ ወታደራዊ ሲቪል አመራሮችን ለማፍራት እየሰራ መሆኑን ብርጋዴር ጄኔራል ቡልቲ ታደሰ ገልጸዋል፡፡

## የአምራች ኢንዱስትሪውን ዘርፍ፡- ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሲንጋፖር፣ የቪዬትናምና ጃፓንን ተሞክሮ ተወስዷል። በሌላ በኩል አምራች ዘርፉን ለማነቃቃት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስደው ያልተሳካላቸውን የሌሎች አገራትንም ተሞክሮ ጭምር ታይቷል ብለዋል።

የየአገራቱ ልምድ በአግባቡ ከተቀመረ በኋላ ወደስራ ተገብቷል። በዚህም ንቅናቄ በተለያዩ ክልሎች ከተጀመረ በኋላ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን ሁሉም አመራር እንዲቀርፍ በማድረግ ዘርፉ እንዲነቃቃ የሚያደርግ ስራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አሁን ላይ የመከላከያ አልባሳትን የተማሪዎች ጫማና አልባሳት እንዲሁም ፈርኒቸሮችን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል ስራ ተጀምሯል፤ በተመሳሳይ በሌሎች ዘርፎችም የአገር ውስጥ ምርትን ከማሳደግ ባለፈ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ዕድል ማመቻቸት ላይ ያተኮረ የንቅናቄ ስራ እያከናወን ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚከናወን ሳይሆን በየዓመቱ የሚካሄድና ዘርፉን ለማሳደግ እንደአንድ አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ መድረክ ነው ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

‹‹የአምራች ዘርፍ አሁን ካለበት አገራዊ ድርሻ ከፍ ማድረግ ይቻላል፤ ለዚህም ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር፣ የአገር በቀል ምርቶችን ተወዳዳሪ በማድረግ፣ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወን ዘርፉ ላይ የሚታዩ ችግሮችን መፍታት እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የአምራች ኢንዱስትሪ ድጋፍ ማድረግ ይገባል›› ብለዋል።

በ10 ዓመቱ የልማት ግብ መሰረት አምራች ዘርፉን አሁን ካለው 6 ነጥብ ስምንት በመቶ የጂዲፒ ድርሻ ወደ 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ ንቅናቄው ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

ዘላቂነት ባለው መልኩ አምራች ኢንዱስትሪውን በመደገፍ አቅሙን ማጠናከር ይገባል። በዚህም አሁን ላይ ያለውን የ50 በመቶ የኢንዱስትሪ ምርታማነት ወደ 85 በመቶ ለማሳደግ የተደራጀ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

የስራ ዕድል ፈጠራውን በተመለከተ በአምራች ዘርፉ አሁን እየፈጠርን ያለው በጣም ትንሽ በመሆኑ በአስር ዓመት መጨረሻ ወደ አምስት ሚሊዮን የማሳደግ ግብ አለን።

ከኤክስፖርት ዘርፍ ጋር በተያያዘ ከአምራች ዘርፉ በየዓመቱ እየተገኘ ያለው 400 ሚሊዮን ዶላር ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ዘርፍ ወደ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር የሚገኝበት ዕድል ስላለ እዛ ላይ ለመድረስ ስራዎች መጀመራቸውን ተናግረዋል ።

መንግሥት የአምራች ዘርፉን ለመደገፍ የሰጠው ትኩረት ጠንካራ ነው። ይህንንም ለኢንቨስትመንት የሚሆኑ የመሰረተ ልማት አቅርቦቶችን በማሳደግና የህግ ማዕቀፎች በማውጣት እያሳየ መሆኑን ገልጸዋል።

አምራች ኢንዱስትሪው እንደ አገር የኢኮኖሚ ሽግግሩን ዕውን ለማድረግ ተስፋ ከተጣለባቸው ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት የተያዘ መሆኑን ገልጸዋል።

ስለኢኮኖሚ በምናወራበት ጊዜ ግን አንድ ጉዳይ ላይ በማተኮር ብቻ የአገራችንን ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ይታወቃል። አምራች ኢንዱስትሪውን ስናሳድግ በተመሳሳይ የግብርና ዘርፉም ሆነ የቱሪዝም አገልግሎት ዘርፎች ያሉንን ዕድሎች አሟጠን መጠቀም አለብን ብለዋል።

## ‹‹ባለሀብቶች..

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡ ወደ ከተማዋ ለሚመጡ የኢንቨስትመንት አልሚዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን ሲሉ የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሰሞኑን ያዘጋጀው ስለኢትዮጵያ የተሰኘው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና የፓናል ውይይት በተካሄደበት ወቅት አቶ ከድር ጁሃር፤ ድሬዳዋን ለኢንቨስትመንት አማራጭ ምቹ ለማድረግ አስተዳደሩ ዘርፍ ብዙ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

አልሚዎች ለኢንቨስትመንት አማራጭ ምቹ ወደሆነችው ድሬዳዋ ከተማ ቢመጡ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ ያሉት ከንቲባው፤ በአምራች ኢንዱስትሪም ዘርፍ የሚሆን የሰው ኃይል በከተማዋ አለ በተጨማሪ በአግሮ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ምቹ የሆነ የአየር ንብረትና የጭነት አገልግሎት አማራጭ መሆኑን ተናግረዋል።

ድሬዳዋ ካላት የባቡርና የዓለም አቀፍ አውሮፕላን የካርጎ ጭነት አማራጭ ውጪ ለጅቡቲ ወደብ ያላት 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ያደርጋታል። ከተማዋ ደረቅ ወደብ አላት። አንድ አልሚ በተሽከርካሪ ከአራት እስከ አምስት ሰዓት ብቻ በመጓዝ ወደውጭ ለመላክም ሆነ ግብዓቶቹን ለጅቡቲ ማስመጣት ይችላል ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ በከተማዋ ያለው የከርሰ ምድር ውሃ ለአልሚዎች አስፈላጊውን የውሃ አቅርቦት ለማመቻቸትና የተጣራ ውሃ ማሸግ ስራ ላይ ለመሰማራት እንደሚረዳ ገልጸዋል።

በአስተዳደር ደረጃ በተደረገው ጥናት መሰረት ድሬዳዋ ላይ 11 አይነት የማኑፋክቸሪንግ አይነቶች ማልማት ይቻላል ያሉት ከንቲባው፤ በተለይ በጨርቃ ጨርቅና ቡና ፈጭቶና አሽጎ ወደውጭ በመላክ ዘርፍ መሰማራት የሚቻልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ገልጸዋል።

በማዕድን ዘርፍ እንዲሁ በሲሚንቶ፣ ኖራና ጀሶና ሌሎች ውድ ማዕድናት ላይ ለሚሰሩ ፋብሪካዎችም አስፈላጊውን ግብዓትና አማራጭ በከተማዋ ዙሪያ በስፋት እንደሚያገኙ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ሆቴልና ቱሪዝምን ጨምሮ በሰባት የአገልግሎት ዘርፎች እንዲሁም በግብርና ዘርፍ ስድስት ዘርፎች ላይ በድሬዳዋ ማልማት የሚቻልበት ዕድል እንዳለ በጥናት ተረጋግጧል፤ በተለይ በግብርናና እንስሳት ሃብት ዘርፍ ለአሳማ ማርቢያና ማቀነባበሪያ የሚሆን ምቹ የአየር ንብረትና የስራ ቦታ በከተማዋ አለ ሲሉ አስረድተዋል።

ለማልማት ለሚመጡ ባለሃብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፤ በተለይ ኢንቨስትመንቱ ውጤታማ እንዲሆን ስራዊችን የሚያጓትቱ ቢሮክራሲዎችን ማስቀረትና አመራሩ በማንኛውም ሰዓት አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ይታመናል። በዚህ ረገድ የድሬዳዋ አስተዳደር ያለው ዝግጁነት ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ የከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን የመስሪያ ቦታ፣ የፍቃድና የመሰረተ ልማት አማራጮችን በማስፋት አልሚዎችን ለመቀበል ዝግጅት አድርገናል ሲሉ አስታውቀዋል።

በከተማዋ ካለው የኢንዱስትሪ ፓርክ በተጨማሪ አስተዳደሩ የእራሱን መጠነኛ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ማዘጋጀቱንም ገልጸዋል።

እንደ ከንቲባ ጁሃር ገለጻ፤ የድሬዳዋ አስተዳደር ከአጎራባች ክልሎችና ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት የፋይናንስ አቅርቦት የሚያመቻቹ ተቋማት ጋር አብሮ ይሰራል።

አመራሩም በመሰረተ ልማት ቅንጅት ትኩረት እንዲሰጥ፣ አሰራሩን በማሻሻልና የኢንቨስትመንት ስራው ውጤታማነት ላይ የእኔም ድርሻ አለ የሚል አመለካከት እንዲይዝ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ ከተማዋ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ ሰላም እንዲኖራት ህብረተሰቡንና የሃይማኖት አባቶችን ያሳተፈ የጸጥታና ደህንነት ስራ መከናወኑን ከንቲባው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጊዜው የሚጠይቀውን ለመስጠት የተዘጋጀን እንሁን!

ኢትዮጵያ፣ ምንም እንኳን በርካታ የውስጥ ባንዳዎችና የውጭ ጠላቶቿ ለውድቀትና ድክመቷ እንቅልፍ አጥተው የሚያሴሩባት፤ ከፋ ሲልም ወግተው የሚያደሟት ቢሆንም፤ ሰጎን ዐይኗን ከእንቁላሏ ላይ ለአፍታም እንደማትነቅል ሁሉ ዘወትር ሁሉ ነገራቸውን ሰጥተውና ያለ እረፍት ቆመው የሚጠብቋት እልፍ ጀግና ልጆች አሏት። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ከፍታዋ በኢትዮጵያውያን እጅ ላይ ስለመሆኑ ተደጋግሞ የሚነገረው። አገር በልጆቿ ትጠበቃለች፤ ትለማለች፤ ትበለጽጋለችም። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን እውነት ነው።

ኢትዮጵያ ትናንትን በወራሪዎች፤ ዛሬ ደግሞ ለውጭ ጠላት ተላላኪነት ባደሩ ባንዳዎች ስትወጋና ስትደማ፤ ኢትዮጵያውያንም ለህልውናቸው ዋጋ ሲከፍሉ ኖረዋል። ይህ ታሪክ የማይዘነጋውና በደማቅ ቀለም ተከትቦ የሚኖር የኢትዮጵያ አርበኞች ገድል፤ ዛሬም በልጆቹ ዘመን በዚህ ትውልድ ደምቆ የራሱን አኩሪ ታሪክ እየጻፈ ይገኛል። ይህ የታሪክ ገጽ ለመጻፉም እንደ ጥንቱ ሁሉ አገር ጀግኖቿም፤ ተላላኪ የእናት ጡት ነካሽ ባንዳዎችም እንደየፈርጃቸው ተከሰተውባት በመታየታቸው ነው።

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ፤ ኢትዮጵያ ጀግኖችን ወልዶ ያሳደገ ማህጸኗ፤ የጠቡትን ጡት የነከሱ፣ የተኙበትን ማህጸን ወግተው የሚያደሙ፣ የበሉበትን ወጪት ረግጠው የሚሰብሩ ለጠላት አዳሪና ተላላኪ ባንዳዎችን አፍርቷል። በዚህም በጀግኖቿ ገድል ኮርታና ቀና ብላ መሄድን፤ በባንዳ ተላላኪዎችም ተወግታ ማንባትን ተለማምዳዋለች። ይሁን እንጂ መወጋትና ማንባቷ ዘወትር በቁርጥ ቀን ልጆቿ ታብሶ የሚሽር፤ ጠባሳው እንኳን እንዳይሰማት አድርጎ የሚጠግን እንደመሆኑ ዛሬም በሕልውናዋ፣ በከፍታዋና በገናና ታሪኳ ምሕዋር ላይ ለመኖር ችላለች።

ይህ ታሪክ ጠገብ ማንነቷ፤ የገናና ጥበብ አውድነቷ፤ የዳግም ከፍታ ጉዞዋ፤ የአፍሪካ ቀንዲልነት የጥቁር ሕዝቦች ፋናነቷ ዛሬም እያገረሸ ለሌሎች ብርሃንን ማሳየት መጀመሩ ለውጭ ጠላቶቿ እረፍት፤ ለውስጥ ባንዳዎቿ ሰላም አልሰጣቸውም። እናም እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በሃሳብም፣ በምግባርም ተባብረውና ተናብበው እጃቸውን አነሱባት። ለሕልማቸው መሳካትም ሕወሓት ይሉት አሸባሪ እንግዴ ልጅ ከልጆቿ መሃል ተፈጥሮ «የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ» ይሉት ብሂል ማሳለጫ የኮርቻቸው ማሳረፊያ ሆኖ እናቱን የሚወጋ፤ ወገኖቹን የሚያደማ አሜኬላን በሁሉም መስክ እየደገፉት አሰማሩባት።

ይሄን የተገነዘቡት የአባቶቻቸው ልጆች የቁርጥ ቀን ጋሻዎቿም እርሷን ለመጠበቅ የማያንቀላፉ፤ ሕልውናዋን ላለማስደፈር እስከ ሞት ዋጋ ሊከፍሉ የተዘጋጁ ናቸውና ሽብር ጋላቢውን ከፈረሱ ለማውረድ፤ ፈረሱንም ወደ ጋጣው ለመመለስ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ጦርነቱንም፣ ዲፕሎማሲውንም፣ ፕሮፖጋንዳውንም በየአውዱ ተሰልፈው እንደ አመጣጡ መልሰውታል። ከድላቸው ማግስትም አገራቸውን ለማልማት፣ በባንዳ ጠላት የወደመውን መልሶ ለመገንባት፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች ምኞታቸው ምን እንደሆነ ያውቁ ስለነበርም ከልማትና መልሶ ግንባታቸው ጎን ለጎን ዳግም ሊመጣ ስለሚችለው ማናቸውም ነገር ራሳቸውን ለማዘጋጀት ቃል ገብተዋል።

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ጠላቶች እና ተላላኪ ባንዳዎቻቸው ይህ እውነት እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም የሚዋጥላቸው አልነበረም። ለምን ቢሉ፤ የጠላት ግብ ኢትዮጵያ ስታሸንፍ ማየት ሳይሆን ስትዳከም፣ ካልሆነም ስትጠፋ ማየት ነው። እናም ከሽንፈታቸው ማግስት ለሌላ ዙር ጦርነት ራሳቸውን ማዘጋጀት፤ አሸባሪው ሕወሓትም የውስጥ የቤት ሥራውን መከወን ጀመረ። ለዚህም የትግራይ ወጣቶችን እያስገደደ ለጦርነት መመልመል፤ በሕዝብ ስም ወደክልሉ የሚሄድ ሰብዓዊ ድጋፎችን ከሕዝብ ጉሮሮ በመንጠቅ ለታጣቂዎቹ በማከፋፈልና በማከማቸት፤ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨትና ለክፉት ተግባሩ ባደራጃቸው የውጭም የውስጥም ተላላኪዎቹ ዓለምአቀፍ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚያስችሉትን የዲፕሎማሲና ፕሮፖጋንዳ ተግባራትን ለማሳካት እንዳቅሙ እየተፍጨረጨረ ይገኛል።

አንድ ጊዜ ስለሰላምና ድርድር፤ ሌላ ጊዜ ስለ ጦርነት፤ ሌላ ጊዜ ሌላ የማይጨበጥ ምኞት ይዞ የሚቅበዘበዘው ይህ የሽብር ቡድን፤ በተለያየ ጊዜ አፍኖ የያዛቸውን ጥቂት የመከላከያ ሰራዊት አባላት፤ የመከላከያ ሰራዊት ቤተሰቦች፤ ለወረራ በተሰማራባቸው ጊዜያት ጠልፎ የወሰዳቸውን ሾፌሮችና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች «ምርኮኛ የመከላከያ ሰራዊት ናቸው» በሚል ከሰሞኑ ለቀቅሁ ብሎ አጀንዳ ለማድረግ ሞክሯል።

ይህ የቡድኑ የተለመደ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ ራሱን ከማሞኘት በዘለለ ውሃ የሚቋጥር ውጤት አያስገኝለትም። ከዚህ ጎን ለጎን በኢትዮጵያውያን መካከል የሃሰት ወሬን በማባዛት እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩና አንድነታቸውን እንዲሸረሽሩ የማድረግ የኖረ ሴራውን ቀጥሏል።

እነዚህ ደግሞ የሦስተኛ ዙር የጦርነት ፍላጎቱን ለማሳካት እና ከቻለም ጦርነቱን ለማሸነፍ ያስችሉኛል የሚላቸውን ቅድመ ዝግጅቶች የማሳለጫ ስልቶቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አሁናዊ ቁመና እንኳንስ ለሕወሓት ዓይነት አሸባሪ ስብስብ ቀርቶ ለሌላውም ማናቸውም የውጭ ወራሪ የሚበገር አለመሆኑን ተገንዝቧል። ይሄን ጠንካራ ቁመና የፈጠረ መከላከያ ሰራዊት ለማሸነፍ ደግሞ ቀድሞ ደጀኑን ሕዝብ አንድም እርስ በእርሱ ማጋጨት፤ ሁለተኛም ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር መነጠልና ሰራዊቱን ደጀን ማሳጣት ሲችል መሆኑን ተገንዝቧል።

ለዚህም ይመቸው ዘንድ ነው በጦርም፣ በፕሮፖጋንዳና ዲፕሎማሲው መስክ ዳግም መንቀሳቀስ መጀመሩ። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያውያን የማንቂያ ደወል ሊሆን የሚገባው ሲሆን፤ ከድል ማግስት «እናልማ፣ የወደመውን መልሰን እንገንባ፣ ለማንኛውም ነገር እንዘጋጅ» ሲል የገባውን ቃል እንዲያስታውስ የሚያደርገው፤ ወቅቱ የሚጠይቀውን ለመስጠትም መላው ኢትዮጵያዊ በየተሰማራበት የተዘጋጀ እንዲሆን የሚያስገድደው ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ከግጭት የሚተርፍም የሚያተርፍም የለም

ይቤ ከደጃች.ውቤ

የአገራችን ሕዝብ በዓለም ላይ አማኒያን ተብለው በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠቀሱት አገሮች ፊታውራሪው ነው። በዓለም በርካታ የእምነት ተከታይ አላቸው ከሚባሉት እምነቶች ዋና ዋናዎቹም በዚህችው አገር ይገኛሉ። እንደ አማኝነታችን ምን አተረፍን? የሚለው ነገር ሲነሳ ግን አጠያያቂ እና ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ይታያል። እምነት ቆም ብሎ ማሰብን በሰው ልጅ ላይ አለመጨከንን ቢያስተምርም፣ እኛ ግን እንደ አማኝነታችን ይሄን አምላካዊ ትዕዛዝ ስንፈጽም አንታይም።

ሆኖም አማኝነታችን እርስ በርስ ከመናቆር ሊያወጣን በተገባ ነበር። እኛ ግን እርስ በእርስ የሚያቆራቁስ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ በእምነት ተቋሞቻችን ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ፤ የአማኞችም ወደ ቤተ እምነቶች ዘወትር መሄድ ከእግር መመላለስ የዘለለ አይሆንም። ይህ ደግሞ በሌሎች የጎጥና ማንነት ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ግጭቶችና ችግሮች አዲስ የመሸጋገሪያ አውድ እንዲሆን እያደረገው ይገኛል።

ምክንያቱም ዛሬ ላይ በየቦታው ሲያቆጠቁጥ የነበረው ማንነትን መሠረት ያደረገው ግጭት መቋጫ አላገኘም። የውስጥ ባንዳዎች፣ የውጭ ጠላቶች ይሄንን አውድ ደጋግመው ለእኩይ ዓላማቸው ሊያውሉት ሲሞክሩ ይታያል። ሆኖም የማንነቱ የግጭት አውድ ለውጭ ጠላቶችም ሆነ ለባንዳዎች የሚፈልጉትን ያህል እልቂት ስላላመጣ አቅጣጫቸውን እየቀየሩ ነው። ይህ ተቀያሪ የትኩረት አውድ ዜጎችን በእምነት ሰበዝ ማጋጨት ነው። ይሄንንም በየቦታው እየሞካከሩ ይገኛል።

በዚህ መልኩ የእምነት ሰበዝ እየተመዘዘ ሕዝብን ማጋጨት ደግሞ ችግሩ ብዙ ነው። ምክንያቱም የእምነት ሰበዝ ግጭት ቢመዘዝ ቢመዘዝ አያልቅም። በዚህ ዓይነቱ ግጭት የሚሳተፍ ማንም አይተርፍም፤ አያተርፍምም። የእምነት ተኮር ግጭት ሁሉም ተያይዞ ተጠላልፎ የሚወድቅበት እንደመሆኑም ቆም ብሎ ማሰብ እና ከዚህ ተግባር መታቀብ የተገባ ነው። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በአንዳንድ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረውን ሃይማኖት ታከክ ግጭት አስመልክቶ በጎንደር ተሰብስቦ ነበር። የጉባኤው አባላት በጎንደር ከተማ በግጭቱ ምክንያት የተጎዱ ቤተሰቦችን በማፅናናት የደረሰውን የንብረት ጉዳት ተዘዋውረው ተመልክተዋል፤ ድርጊቱንም አውግዘዋል።

የጉባኤው ጠቅላይ ፀሐፊ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንደተናገሩት፤ በጎንደር ከተማ በሃይማኖት ሽፋን የተፈጠረው ግጭት የእምነት ተቋማት ግጭት ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም። በግለሰቦችና ቡድኖች የተጀመረን ግጭት በሃይማኖት ተቋማት በማላከክ ሽፋን መስጠት ተገቢነት የለውም። የእምነት ግጭት ማሳያም ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። በየትኛውም ቤተ እምነት ውስጥ ግጭትን፣ መገዳደልንና አንዱ አንዱን እንዲያጠፋ የሚፈቅድ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ የለም። እናም በሌለ መሠረት ላይ ሆነው ነው ጠላቶቻችን በእምነት ተቋማትና አማኞች መካከል ግጭት የቀሰቀሱት። የእምነት ተቋማትንና አማኒያንን ተገን በማድረግ ግጭት በመቀስቀስ አፍራሽ ተልዕኮን ለማሳካት መሞከር ደግሞ በሕዝብና አገር ላይ ጥሎት ከሚያልፈው ጠባሳ በዘለለ የሚያስገኘው ትርፍ የለም። እናም በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል።

የኢትዮጵያውያን ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ጠንካራ ትስስር የሚስተዋልበት ቢሆንም፣ ጠላቶቻችን ይህን ትስስር ለማስለል አልፎም ተርፎ ለመበጠስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። አንዳንዶች በተለያዩ ጊዜያት በአገራችን የታዩ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በመመልከት የአገራችንን ዕጣ ፈንታ እንደ ሶሪያ ሊቢያና ጎረቤታችን ሶማሊያ ሲመለከቱት ይስተዋላል። የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መሠረቶች ሲታዩ ይህ ሊሆን የሚችልበት ዕድል የለም፤ ጠላቶቻችን ግን ይህን ዕድል ለመፍጠር ያልከፈቱት ዘመቻ የለም። እንዲያም ሆኖ ግን ግጭቶች ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ለየትኛውም አለመግባባትና ግጭት ዕድል ሊሰጥ ለሚችል ጉዳይ መዘናጋትና ቦታ መስጠት አይገባም። ጠብ ጫሪዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማድረግ ይገባል።

የእምነት ግጭትን ከዳር ሆነው የሚለኩሱና የሚያቀጣጥሉ፣ ይሄን ተቀብለውም የሚያራግቡ አገራቸውን ከመጉዳት በቀር የትም እንደማያደርሳቸው መረዳትና ከጎሊናቸው ጋር መታረቅ ይኖርባቸዋል። ከእንዲህ ዓይነት አውሬያዊነት እንዲርቁ እንመክራቸዋለን። ሰው በመግደልም ሆነ የእምነት ተቋማትን በማውደም የሚያገኙት ጥቅም የለም፤ አትርፈናል የሚሉ ከሆነም ትርፋቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ የማይሽር ቁስል ማስቀመጥ ይሆናል። ይሄ ደግሞ ምንም አይጠቅምም። ያስጠይቃል፤ በታሪክም ተወቃሽ ያደርጋል።

ሆን ተብሎ በእምነት ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ ግጭቶችን፣ ሞትና ማፈናቀሎችን፣ እንዲሁም የእምነት ተቋማትን ማውደምን ተመልክተናል። በዚህ ረገድ በእምነት ተቋማት ግጭት እንዲባባስ የሚሠሩ የየእምነቱ ጽንፈኞች እንዳሉም ይታወቃል፤ ከፊሎቹ ለሚፈጥሩት ግጭት ስፖንሰር አላቸው። ይሄን ከውጭ ሆነው ለሚደግፉ ኃይሎች ደግሞ በየትኛውም መንገድ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀሰቀስ ግጭት ደግሞ ሠርግና ምላሻቸው ነው።

ከእነዚህ ግጭት ናፋቂዎች ከፊሎቹ የየእምነቱን ማዕረግ ያደረጉ ናቸው። እነዚህ እንደ አማኝ የአማኝ ቋንቋ እየተናገሩ ሕዝቡን ግጭት ውስጥ ይከታሉ። ገሚሶቹም በምርጫ ወቅት ብቻ ብቅ የሚሉ ጎርፍ አመጣሽ ሊባሉ የሚችሉ ፓርቲዎች ናቸው። ጎርፍ አመጣሽ ያልኩት ምርጫ ሲመጣ ሲመጣ የሚቋቋሙ ምርጫው ሲወጣ ደግሞ የሚከስሙ ሆነው ድምፃቸውን የማያሰሙ፤ የራሳቸውን የፖለቲካ ሥራ በአግባቡ መሥራት የተሳናቸውና የገዥው ፓርቲ ክፍተቶችን የሚያራግቡ ናቸው።

እነዚህ ፓርቲዎች ድምፃቸውን አጥፍተው ቆይተው ግጭቶች ሲካሄዱ ተቆርቋሪ መስለው መግለጫ ይሰጣሉ። ግጭቱን በባሌም በሉት በቦሌ ቢስፋፋ እንደ ሠርግና ምላሽ አድርገው ይቆጥሩታል። በእዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ ለፀቡ አሉባልታ እየነዙ በአማኞች መካከል ጦር ሊያማዝዙ የሚፈልጉ ጋዜጠኞችና የማህበራዊ ሚዲያዎችም አሉ። በመሆኑም ይሄ ሕገወጥነት የተከፈለው ዋጋ ተከፍሎ መፍትሄ ማግኘት ይኖርበታል። ጥፋትን በጥፋት ለመመለስ የሚሠሩ አደብ እንዲይዙ ማድረግ፤ ለተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የሆኑም ሆኑ በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላትም ተለይተው በሕግ ተጠያቂ ሊደረጉ ያስፈልጋል።

ገዥው ፓርቲም ዜጋው ሁሉ መንግሥት አድርጎ የመረጠው ልማት ያመጣልናል ሰላም ያሰፍንልናል ብሎ እንጂ ሁከትና ሞት ሲፈበረክ ቆሞ እንዲመለከት አይደለም። ከነበሩት ፓርቲዎች የተሻለ ስለሆነ አሸነፈ፤ አሁንም አመራሩ በሰላሙ የተሻለ ሆኖ ይገኝ። ይህ ደግሞ አንድም የሚረጋገጠው የሕግ የበላይነትን ማስጠበቅ ላይ ነው። እዚህ ላይ ክፍተት እየታየ በመሆኑ ለይቶ ለመፍትሄው መሥራት ይኖርበታል። ምክንያቱም፤

**« ፊት ነበር እንጂ መጥና መደቆስ**
**አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ»**

እንደሚባለው አገርኛ ስነ ቃል ግጭት ከደረሰ በኋላ መግለጫ መስጠቱ ምንም አይፈይድም። የፀጥታ አካላቱ ቀዳሚ ሥራ አደጋ መተንተንና መገመት፤ አደጋን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተጠንቀቅ መቆም ካልሆነ በየጊዜው አደጋ መድረሱ የዘወትር ክስተት ይሆናል። ኢንቨስተር መሳብ፣ ቱሪስትም ሆነ ዳያስፖራ ወደ አገር መጥቶ ዶላር መመንዘርና መዘርዘር የሚቻለው ሰላማችን አስተማማኝ ሲሆን ነው። የአገር ውስጡም ባለሀብት መሥራትና ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችለው አስተማማኝ ሰላምና ፀጥታ ሲኖር ነው።

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ከስህተቶቻችን መማር ለምን አቃተን?

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ስለ ለውጥ ሕግ እናወራለን። የለውጥ ሕግ የሕይወት ሕግ ነው። የሕይወት ሕግ ደግሞ የአጠቃላዩ እንቅስቃሴአችን ሕግ ነው። ሕይወት ሶስት ቀን ናት.. ትላንት ዛሬና ነገ ስል ተነስቻለሁ። ትላንት ዛሬን የምናደምቅበት ብዕራችን ነው ስል ቀጥያለሁ። ነገ ደግሞ ምን እንደሆነ የማናውቀው ለእያንዳንዳችን ባዳ ቀን ነው ስል ሰልሻለሁ። እኚህ ሶስት የጊዜ ፈረቃዎች በሕይወታችን ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ እየገለጥን እናያለን። ዓለም ሁለት ዓይነት ሰዎች አሏት፤ ከትላንት የሚማሩና ትላንትን የሚያማርሩ። ከትላንት የሚማሩ ሁሌም አሸናፊዎች ናቸው። የዚህን ዓለም ብርቱና ስኬታማ ሰዎች ብታስተውሉ በትላንት ተምረው ዛሬን መልካም ያደረጉ ናቸው። በእኛ አገር እየሆነ ያለው ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው። ትላንትን ለመማረሪያ እንጂ ለመማሪያ ስናደርገው አንታይም። የዛሬ ችግሮቻችንን ከትላንት አብራክ ውስጥ ጎርጉረን ያወጣናቸው ናቸው። በትላንት የዛልን፣ በትላንት የምንኖር ሕዝቦች ነን። ሰው ትላንትን መርሳት ካልቻለ ዛሬ አይኖረውም። ሰው መኖር የሚጀምረው ትላንትን መርሳት ሲችል ብቻ ነው።

ትላንት ከትዝታ ባለፈ በእኛ ሕይወት ላይ ሕላዊነት የለውም። አብዛኞቻችን በትላንት ዛሬን የምንኖር ነን። ለዛም ነው እንደ ሃገር ከስረን የቆምነው። ትላንት ለዛሬ የሚሆን ጉልበት የለውም። እንድንማርበትና ዛሬን መልካም እንድናደርግበት መጥቶ የሄደ እንጂ በቁጭትና በሮሮ እንድናስታውሰው ሆኖ የተፈጠረ አይደለም። እኛ ኢትዮጵያውያን ከትላንት ብንማር የሚያስተምሩን በርካታ ታሪኮች ነበሩን። ግን አንማርም፤ ዛሬን በትላንት መንፈስ የምንኖር ነን። በትላንት ጉያ ውስጥ የተደበቁ ብዙ የአንድነት ታሪኮች፣ ብዙ የመለያየት ታሪኮች አሉን። የሚጠቅመንን እየወሰድን የማይጠቅመንን መተው አናውቅበትም። ዛሬዎቻችን በትላንት ቁርሾ፣ በትላንት የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም የተጨማለቁ ናቸው። አዲስ ዛሬ መፍጠር አልቻልንም። ሰው ከትላንት ተምሮ አዲስ ዛሬን መፍጠር ካልቻለ ሕልውናውን አደጋ ላይ እየጣለ ነው የሚሄደው። ስህተት የሰውን ልጅ ካለወጠው በምንም አይለወጥም። ትላንት መጥቶ የሄደው እንድንማርበት ነው። በትላንት ችግሮቻችን መማር ካልቻለን የምድርን ትልቁን የለውጥ ሕግ ዘንግተናል ማለት ነው።

ለምን ስልጣኔ የራቀን ይመስላችኋል? ፊት ተፈጥረን ለምን ኋላ የቀረን ይመስላችኋል? ለዛሬ የሚሆን አዲስ ልብ ስለሌለን ነው። ችግሮቻችንን ችግር ፈጣሪ በሆነ ሀሳቦቻችን ለመፍታት ስለምንሞክር ነው። በመሠረቱ ችግር.. ችግር ፈጣሪ በሆነ ጭንቅላት አይፈታም። የመፍትሔ ስፍራው ምክንያታዊ አዕምሮ ነው። ጭንቅላታችን በትላንትና በአምና የፖለቲካ አስተሳሰብ ተመርዞ፣ በትላንት የታሪክ ቁርሾ ተይዞ ከፍ ማለትም ሆነ ለችግሮቻችን መፍትሔ መውለድ አንችልም። ለአስተዋይ ሰው በስህተት ውስጥ መፈጠር ልክ በሆነ ነገር ላይ ከመፈጠር የበለጠ አዋጭ ነው። ብዙዎቻችን ስህተት የሚያበላሸን እንጂ የሚሞርደን አይመስለንም። ለዚህም ነው በእውቀት ድርቀት የምንሰቃየው። ስህተት ዋጋ ቢስ የሚሆነው የማንማርበትና የማንለወጥበት ከሆነ ብቻ ነው። ዕውቀት የትም አለ፣ የሰው ልጅ የትም፣ በማንም ሊማር ይችላል። በስህተት ውስጥ የመማርን ያክል ዕውቀት ግን የትም አይገኝም። እንከን አልባ እውቀት አንድ ጊዜ ነው የሚቀርጸን የስህተት እውቀት ግን እድሜአችንን ሙሉ የሚከተለን ፍጹምናችን ነው። እኛ ግን ከስህተቶቻችን አንማርም። ትላንትን ዋና የችግሮቻችን ምንጭ አድርገን የምንገልጥ ነን። ስህተት ካልተማርንበት ሌሎች ችግሮችን እየፈጠረ የመከራ ሎሌ ነው የሚያደርገን። የሰው ልጅ ደግሞ ትላንትን እያስታወሰ እንዲቆዝም ሳይሆን በዛሬ በረከት ተደስቶ ተመስገን እያለ እንዲኖር ነው ሰው የሆነው።

በሕይወታችን የትኛውም ቦታ ላይ በስህተት ውስጥ ካላለፍን ምሉዕ አንሆንም። ሳንገዳገድ መቆም አንችልም። በአንድ ነገር ላይ የበላይ ስንሆንና ኃይልን ስንላበስ የትም ቦታ ላይ ያለአንዳች ተግዳሮት እንፈስሳለን። ይሄ ደግሞ በስህተት ውስጥ የመፈጠር ልዕልና ነው። አንዳንዶች በችግራቸው ሌላ ችግር

በብዙ ስህተት ውስጥ አልፈን ነው ዛሬን ያየነው። ስህተት ውስጥ ጥበብ አለ። ውድቀት ውስጥ መስፈንጠር አለ። እኛም ከትላንት እየተማርን፣ ካለፈው እየተረዳን ዛሬን በዋጋ መኖር ግድ ይለናል። ጠቢብ ሰው ማለት መከራ የማይደርስበት ማለት ሳይሆን ከመከራው ተምሮ አዲስ ዛሬን የሚፈጥር ማለት ነው። እኛስ ምን ዓይነቶች ነን?..

ይፈጥራሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ በችግራቸው ነጋቸውን ብሩህ ያደርጋሉ። በችግራቸው ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች የዕውቀት ባይተዋር ናቸው። በችግራቸው የሰላምን ግንብ ገንብተው የሚኖሩ እነሱ ደግሞ መለኛ ናቸው። እኛም ለድህዋ ሃገራችን መለኛ መሆን ይጠበቅብናል። በችግራችን ላይ ሌላ ችግር ሳይሆን ችግሮቻችንን የምንሽርበት የመነጋገርና፣ የመወያየት ብልሀትን የእኛ ማድረግ ይጠበቅብናል። መንግሥት እንደ መንግሥት፣ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ከችግሩ ተምሮ ለሰላም የሚሆን አቅም፣ ለአንድነት የሚሆን ኃይል ማጎልበት አለበት። ጥበቦቻችን በትላንት አስተሳሰብ ታውረው የዛሬን በረከት ማየት ካልቻሉ እንደ ለመድነው ከጦርነትና ከመጠላላት አንወጣም። ጦርነትና እኔነት ባህላዊ ጨዋታችን እስኪመስሉ ድረስ ለዘመናት ኖረንባቸዋል። ኢትዮጵያዊነት መገዳደል እስኪመስል ድረስ ለዛውም ከወንድሞቻችን ጋር፣ ለዛውም እኛ ከምንላቸው ጋር ደም ተቃብተናል። ሰው በሰላም ዋርካ ስር መጠለል ሲገባው በመከራ ሮሮ ውስጥ መውደቁ ሁሌም ይደንቀኛል። ችግሮቻችን ብልህ እንዲያደርጉን እንጂ ሞኝ እንዲያደርጉን መፍቀድ የለብንም።

ዓለም የስህተት መልክ ናት። ስህተት ነው እንዲህ ጠፍጥፎ ያበጃት። የአሁኑ ውብ መልኳ በስህተት ውስጥ የተፈጠረ ነው። ዓለም የብዙ ትውልዶች አስተሳሰብ፣ የብዙ ሀሳቦች የስህተት ነጸብራቅ ናት። በተለያየ ዘመን የመጡ አስተሳሰቦች፣ በተለያየ ዘመን የመጡ አመክንዮ ሀሳቦች አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ በመሆን የፈጠሯት ናት። እያጠፉ የሳሏት፣ እያደመቁ ያደበዘዟት የልክነትና የስህተት ቅይጥ። ዓለም እኮ ዛሬም ድረስ ተሠርታ አላለቀችም..ዛሬም ድረስ ተስላ አልተጠናቀቀችም። እኛም በብዙ ስህተት ውስጥ አልፈን ነው ዛሬን ያየነው። ስህተት ውስጥ ጥበብ አለ። ውድቀት ውስጥ መስፈንጠር አለ። እኛም ከትላንት እየተማርን፣ ካለፈው እየተረዳን ዛሬን በዋጋ መኖር ግድ ይለናል። ጠቢብ ሰው ማለት መከራ የማይደርስበት ማለት ሳይሆን ከመከራው ተምሮ አዲስ ዛሬን የሚፈጥር ማለት ነው። እኛስ ምን ዓይነቶች ነን?.. የሃገራችን አብዛኞቹ ችግሮች ከትላንት ማህጸን ውስጥ የሚመዘዙ ናቸው። ይህ ማለት ዛሬም ድረስ ከትላንት አስተሳሰብ አልወጣንም ማለት ነው። ይህ ማለት ዛሬም ድረስ እንደትላንቱ ነን ማለት ነው። እንደ ሃገር ከትላንት እኩይ አስተሳሰብ መለየት ይኖርብናል። እንደ ሕዝብ፣ እንደመንግሥት ትላንትን በይቅርታ የሚሻገር አዕምሮና ልብ ልናዳብር ይገባል እላለሁ።

ሰው በዕውቀት ሲዘመን፣ በስልጣኔ ሲቀድም ነገ ላይ በኩራት የሚያወራውን ታሪክ ዛሬ ይሠራል እንጂ በትላንት ጦስ ዛሬን አይኖርም። ዛሬ ለሁላችንም አዲስ ቀን ነው። ስለምንድነው በትላንት ነውር ዛሬአችንን የምናጨልመው? ስለምንድነው በአንድ ዓይነት አስተሳሰብ አንድ ዓይነት ሆነን የምንኖረው? ይሄ ሁላችንም ጠይቀን የምንመልሰው የጋራ ጥያቄአችን ነው። ከትላንት አስተሳሰብ ለመውጣት የዛሬን ዋጋ መረዳት ይኖርብናል። ከትላንት አስተሳሰብ ለመመለስ መንግሥትና ሕዝብ አዲስ ነገር መናፈቅ ይኖርባቸዋል። ከትላንት የጦርነት አስተሳሰብ ለመላቀቅ የትላንትን ቁስል የሚያሽር የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ይኖርብናል። ትላንትን መማሪያ እንጂ መማረሪያ ያላደረገ ትውልድ ሃገራችን ያስፈልጋታል። እኛ ኢትዮጵያውያን ፖለቲካ ያመረቀዘው የብሔር ቁስል አለብን። እኔነትና ተረኝነት የወለደው የመገፋፋት ሕመም አለብን። ራስ ወዳድነትና ጎጠኝነት የጸነሰው የመጠላላት ነቀርሳ አለብን። ከነዚህ ደዌአችን ለመፈወስ ደግሞ ትላንትን ገሎ መቅበር አለብን። ከነዚህ ደዌአችን ለመዳን እንደ ትላንት ያልሆነ አዕምሮና መንፈስ ያስፈልገናል።

ሰው ወደ ትላንት ሲሳብ የዛሬን በረከት አይደርስበትም። ስልጣኔ ሊርበን ይገባል። እድገትና ዘመናዊነት ሊጠማን ይገባል። ይሄን ሁሉ ዘመን ኋላ ቀርተን እንኳን በሌሎች መቀደማችን አይቆጨንም። በማይጠቅመን ነገር ያባከንው ጊዜ ሊቆጨን ይገባል። አንድነት አጥተን የተገፋፋንባቸው ጊዜያቶች ሊያስቆጩን ይገባል። ትውልድ ካልተቆጨ፣ መንግሥት ካልተቆጨ፣ ሕዝብ ካልተቆጨ ከትላንት አስተሳሰብ መላቀቅ አይችሉም። የሃገራችን ሰላም ማጣት፣ የሕዝባችን ኋላ መቅረት፣ የፖለቲከኞቻችን አለመግባባት ሊቆጨን ይገባል። የትውልዱ ብሔር ተኮር አስተሳሰብ፣ በትላንት አስተሳሰብ ዛሬን መኖራችን ሊቆጨን ይገባል። የስኬት ሕግ አስተሳሰብን መሠረት ያደረገ ነው። የለውጥ ሕግ አምናን ሳይሆን ዘንድሮን፣ ትላንትን ሳይሆን ዛሬን የተንተራሰ ነው። እኛንም ሆነ ሌሎችን የምንቀይረው በአስተሳሰባችን ስንቀየር ነው። ሕይወታችንንም ሆነ ሃገራችንን የምንቀይረው ከማይጠቅሙን አፍራሽ አመለካከቶች ስንርቅ ነው። ዛሬ ላይ የሃገራችን መልክ ወያባ ነው። የእርቅና የይቅርታ ሀሳብ አጥታ ሃገራችን ጠውልጋለች። የውይይትና የተግባቦት መድረክ አጥቶ ሕዝባችን ተጎሳቁሏል። ዳገቱን እናልፍ ዘንድ አዲስ አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ከነበርንበት ዝቅታ ከፍ እንል ዘንድ ዕውቀት መር የሕይወት ልምድ ግድ ይለናል።

ሕይወታችንን ከትላንት በመማር እናለምልም። ሃገራችንን ከትላንት በመማር እናሻግር። የዚህ ዓለም ከባዱ ጥፋት ትላንትን ዛሬ ላይ መድገም ነው። ሰው የትላንቱን ጉስቁልና ዛሬ ላይ ከደገመው፣ የትላንቱን ስህተት ዛሬ ላይ ከመለሰው እንደ ትላንቱ ሆኖ ከመኖር ባለፈ አዲስነት አይጎበኘውም። ነውር እየመሰላቸው መሳሳትን አጥብቀው የሚፈሩ ብዙ ሰዎች አሉ። ስህተትን በመፍራት ተጠንቅቀው የሚረግጡ፣ ተጠንቅቀው የሚኖሩ፣ አድብተው የሚንቀሳቀሱ ብዙ ናቸው። እነኚህ ሰዎች ሳያውቁ ራሳቸውን ከጥበብ እያራቁት እንደሆነ ማን በነገራቸው እላለሁ። ስህተትን በመፍራት መናገር ያቆሙ፣ መጠየቅ እርም ያሉ፣ መሞከርና መጀመር የፈሩ ብዙ አሉ። ስህተት አያስፈራም የሚያስፈራው ከስህተት አለመማርና አንድ ዓይነት ሆኖ መኖር ነው። የሚያስፈራው በአንድ ጥፋት ሁልጊዜ እየተጸጸቱ መኖር፣ ሁልጊዜ እያለቀሱ መኖር ነው። የሚያስፈራው በአዲስ አስተሳሰብ ከዘመኑ ጋር አብሮ አለመራመድ ነው። የሚያስፈራው የዛሬን አዲስ ማለዳ በትላንት ጨለማ መሰወር ነው። የሚያስፈራው ሃገርን በአዲስ ልብ፣ ሕዝብን በአዲስ ተስፋ አለማሻገር ነው።

ሕይወት ትምህርት ቤት ናት። ጊዜ ደግሞ መምህራችን። እኛ ደግሞ ተማሪዎች። በዚህ የተፈጥሮ ሂደት ውስጥ ነን። በሕይወት ትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ መሆን ግዴታችን ነው። ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ አለመሆን ማለት ለመውደቅና ለመሸነፍ መዘጋጀት ማለት ነው። ዓለም ደግሞ ለተሸናፊዎች ቦታ የላትም። ዓለም የባለራዕዮች ናት። ዓለም ራሳቸውን ለመቀየር ከሌሎች ጋር ለሚተባበሩ የተገለጠች ናት። ዓለም ተነጋግረው ለሚግባቡ ነፍሶች የተሰጠች ናት። ዓለም በትጋትና በጥረት ከፍ ለማለት ለተሰናዱ የተዘጋጀች ናት። የእኛ ጥሩ ተማሪ መሆን ጥሩ ሃገርና ጥሩ ትውልድ በመፍጠር ሂደት ላይ የአንበሳ ድርሻ አለው። ጥሩ የሕይወት ተማሪ መሆን ማለት ከትላንት ተላቆ ዛሬን ብቻ መኖር ነው። ጥሩ ተማሪ መሆን ማለት ከዘልማድ ወጥቶ እውቀት መር በሆነ እሳቤ ሃገርን ማራመድ ነው። ጥሩ ተማሪ መሆን ማለት ጥላቻን በይቅርታ መሻር ማለት ነው።

በየትኛውም የሕይወት ስፍራ ውስጥ ትልቅ ነገር ለማግኘት ስንነሳ የምናጣው ትንሽ ነገር ይኖራል። ዓላማችን ትልቁን ነገር ማግኘት እስከሆነ ድረስ የምናጣው ትንሽ ነገር ሊያስቆጨን አይገባም። ዓላማችን ሊሆን የሚገባው በትልቅ ሀሳብ ትልቅ ነገር ማግኘት ነው። በይቅርታ ማሸነፍ ነው። ዘመኑ በከሸፈ ሀሳብ የምንራመድበት ሳይሆን በታደሰ ሰውነት አንድነትን የምናጠናክርበት ነው። አሁን ላይ እየባከንን ነው። በትላንት ዛሬን መኖር አልቻልንም። እጃችን ላይ ያለውን ውድ ነገር በርካሽ እየቀየርን ነው። ወርቃችንን በጠጠር እየመነዘርን ነው። ቁራ ለማግኘት ርዕግባችንን እየሸጥን ነው። ምን እንደሚያስፈልገን ማወቅ አልቻልንም። የትላንት ስህተቶቻችንን ዛሬም በመድገም ላይ ነን። ለሰላም ስንደክም፣ ለአንድነት ስንበረታ አንታይም። ችግሮቻችን ሌላ ችግር ሲፈጥሩብን እንጂ ሰላም ሲያወርዱልን አናይም። ታድያ ከስህተቶቻችን መማር ለምን አቃተን? ይህ ለሁላችንም የቀረበ ጥያቄ ነው። አበቃሁ፤ ሰላም!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የቤት ግብይቱን በቴክኖሎጂ

**አንተነህ ቸሬ**

በኢትዮጵያ ዋጋቸው ጣሪያ ነክቶ አልቀመስ ካሉ ዘርፎች መካከል የቤት ግብይት አንዱ ነው። በተለይ በከተሞች እንኳንስ ጥሩ ቤት መግዛት፣ ቤት መከራየትም ለአብዛኛው ዜጋ ቅንጦት ሆኖ እየተስተዋለ ነው። የዚህ ችግር መሠረታዊ ምክንያት የፍላጎትና የአቅርቦት አለመመጣጠን እንደሆነ ቢገለፅም ይህን አለመመጣጠን የሚፈጥሩ ሌሎች መንስኤዎች አሉ።

ከእነዚህም መካከል አንዱ የዘርፉ ግብይት በፍትሐዊ የገበያ ሥርዓት እንዲከናወን የሚያስችል የተቀናጀና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት አለመኖሩ እንደሆነ ይጠቀሳል። ይህ የመረጃ ክፍተት ደግሞ የዘርፉ ግብይትና አስተዳደር መደበኛ ባልሆነ ሥርዓትና ተዋንያን (Informal System) እንዲመራ አድርጎታል። የቤት ፍላጎትና አቅርቦት የተመጣጠነ ካለመሆኑም በተጨማሪ በቤት ግብይት ሥርዓት ውስጥ በቂ የሆነ መረጃ አለመኖሩ ደግሞ ችግሩን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አድርጎታል።

‹‹እፎይ ፕላስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር›› የተባለው ተቋም ይህን ችግር በማቃለል የቤት ግብይትን የሚያዘምን መላ ይዞ ወደ ገበያው መቅረቡን ከሰሞኑ ይፋ አድርጓል። ድርጅቱ ይፋ ያደረገው ቴክኖሎጂ ‹‹እፎይፕላስ ዶት ኮም (efoyplus.com)›› የተሰኘ የድረ-ገፅ አገልግሎት ነው። ዋና ትኩረቱን በቤት ግብይት (ኪራይ፣ ሽያጭና ግዢ) ላይ አድርጎ በገበያ ላይ ያሉትን የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠን የሚያስከትሉ ተግዳሮቶችን የመቀነስ እንዲሁም የኢትዮጵያን የግብይት ሥርዓት የተሳለጠና ውጤታማ ማድረግ መሆኑ ተገልጿል። የእፎይ ፕላስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌትነት ዘመነ የሰጡንን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።

### የቴክኖሎጂው ምንነትና አገልግሎት አሰጣጥ

የቤት ግዢና ሽያጭ ገበያው በዓመት እስከ 400 ቢሊዮን ብር ግብይት የሚከናወንበት እንደሆነ የገበያ ዳሰሳ ጥናቶች ያመለክታሉ። ከዚህ ግብይት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆነው የሚከናወነው መደበኛ ባልሆኑ የዘርፉ ተዋንያን (ባለንብረቶች፣ አሻሻጮች/ደላላዎች) አማካኝነት ነው። በኪራይ የሚከናወነው ግብይት ደግሞ ከዚህም የበለጠ ነው። ይህን ያህል ግዙፍ ገንዘብ የሚዘዋወርበት ገበያ ግን በሚገባው ልክ በሥርዓት እየተመራ አይደለም።

የቤት ፍላጎትና አቅርቦት መመጣጠን ስላልቻለ የቤት እጥረት ይስተዋላል። በኪራይም ሆነ በግዥና ሽያጭ ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት አለ። ይህ ችግር እንዲፈጠር ዋነኛ መንስዔ የሆነው አንድ የተማከለ የግብይት ማዕከልና የመረጃ ፍሰት አለመኖሩ ነው። ይህም አብዛኛው የዘርፉ ግብይትና አስተዳደር መደበኛ ባልሆኑ ተዋንያን እጅ እንዲወድቅ ምክንያት ሆኗል።

በቤት ግብይት ዘርፍ የሚዘዋወረው ይህ ግዙፍ ገንዘብ በሚመጥነው ቴክኖሎጂ የተደገፈ ባለመሆኑ እፎይፕላስ (efoyplus.com) ይህን አሠራር ለማዘመን መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል። ቴክኖሎጂው ጊዜውን የጠበቀና ሰዎች በቀጥታ እንዲገበያዩ ማድረግ የሚያስችል ቀላል ዘዴ ነው።

ይህ የድረ-ገጽ ቴክኖሎጂ ሰዎች በኮምፒዩተራቸው ወይም በስልካቸው አማካኝነት መጠቀም የሚችሉት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የኦንላይን/ድረ ገፅ ተደራሽነት የሌላቸው አካላት ደግሞ በ9793 የጥሪ ማዕከል (Call Center) አማካኝነት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ቴክኖሎጂ ነው። በጥሪ ማዕከሉ በኩል አገልግሎቱን ማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች ዝርዝር መረጃዎችንና ፍላጎቶቻቸውን በማስመዝገብ የግዢና የሽያጭ ፍላጎታቸውን ማሳካት ይችላሉ።

በአጠቃላይ ቴክኖሎጂው የሚከራይና የሚሸጥ ቤት አቅራቢዎችን ከፈላጊዎች ጋር የማገናኘት፣

> **በአገሪቱ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ እያደረጉና በኢኮኖሚው ውስጥ ችግር እየፈጠሩ ከሚገኙ መካከል አንዱ በቤት ግዥና ሽያጭ ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረትና ተገቢ ያልሆነ የገበያ አመራር ነው። በዚህ ዘርፍ በዝርዝርና ሥርዓት ባለው መልኩ የተጠናቀረ መረጃ የለም። እፎይፕላስ ይህን ችግር ታሳቢ በማድረግ የዘርፉን መረጃዎች ወደ ቴክኖሎጂው ቋት እንዲገቡ በማድረግ አገልግሎት ፈላጊዎች ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ ይጥራል።**

የግንባታ ዕቃዎችን የመሸጥና የመግዛት እንዲሁም ቤትን በመግዛትና በመሸጥ ሂደት የውክልና አገልግሎት የመስጠት ተግባራትንም ያከናውናል። አገልግሎት ፈላጊዎች በአቅራቢያቸው የሚገኝ የሰለጠነ አሻሻጭ ከፈለጉም በጥሪ ማዕከሉ በኩል እንዲያገኙም የሚያስችል አሠራርም አለው። አሻሻጮቹም ለአገልግሎት ፈላጊዎች ምክርና እርዳታ ይሰጧቸዋል።

በአገሪቱ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ እያደረጉና በኢኮኖሚው ውስጥ ችግር እየፈጠሩ ከሚገኙ መካከል አንዱ በቤት ግዥና ሽያጭ ላይ የሚስተዋለው የዋጋ ንረትና ተገቢ ያልሆነ የገበያ አመራር ነው። በዚህ ዘርፍ በዝርዝርና ሥርዓት ባለው መልኩ የተጠናቀረ መረጃ የለም። እፎይፕላስ ይህን ችግር ታሳቢ በማድረግ የዘርፉን መረጃዎች ወደ ቴክኖሎጂው ቋት እንዲገቡ በማድረግ አገልግሎት ፈላጊዎች ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ ይጥራል። በዚህ መንገድ በገበያው ላይ አማራጭ ቤቶችን ማቅረብና ያሉትንም ማስተዋወቅ የሚቻልበት መድረክ ይፈጠራል።

ብዙ አሻሻጮች የዋጋ ንረትን በማባባስ ረገድ አስተዋፅኦ አላቸው፤ በተጨማሪም ቁጥራቸው ጥቂት በማይባሉ ባለሀብቶችም ክፍያቸውን ይከለከላሉ። ይህ የሆነው ደግሞ አሻሻጮቹ ኢ-መደበኛ ሆነው ስለሚሠሩ ነው። እፎይፕላስ የቤት ግዢና ሽያጭ ገበያው በመረጃና በሕጋዊ አሠራር ላይ ተመስርቶ እንዲከናወን የማድረግ ዓላማ ያለው በመሆኑ፣ አሻሻጮች (ደላላዎች) ስልጠና እንዲያገኙና ሥራቸውን በፍትሐዊ መንገድ እንዲሠሩ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል። አሻሻጮች ተገቢውን ስልጠና አግኝተውና መረጃ ኖሯቸው የሚሠሩ ከሆነ ጥቅማቸውን ያስከብራሉ፤ ገበያውም በሥርዓት እንዲመራ ሚና ይኖራቸዋል። እፎይፕላስ ይህን እውን የሚያደርጉና አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ደረጃዎች (Standards) ያዘጋጃል።

ቴክኖሎጂውን የማበልፀግ ሥራ ከተጀመረ ቆይቷል። ሃሳቡ የተወጠነው ከሦስት ዓመታት በፊት ነው። ሥራው ከሃሳብነት ተሻግሮ ለትግበራ ከበቃ በኋላም ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል፤ አስተያየቶች ተሰብስበዋል፤ ማሻሻያዎች ተደርገውበታል። በሙከራ ከቆየና ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን ካደረገ በኋላ ይፋ ተደርጎ ለአገልግሎት በቅቷል። ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበ ሕጋዊ ድርጅት ነው።

### የቴክኖሎጂው ልዩ ገፅታዎች

ቴክኖሎጂው መሰል አገልግሎቶችን ከሚሰጡ ተቋማትና አሠራሮች የሚለዩት ባህርያት አሉት። ከእነዚህ ባህርያት መካከል አንዱ ቴክኖሎጂው ሻጭና ገዢን በቀጥታ ማገናኘት መቻሉ ነው። ለዚህ የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ (Service Fee) ዝቅተኛ ነው። አሁን ገበያው ላይ ባለው አሠራር አሻሻጮች ከቤት ኪራይ 10 በመቶ፣ ከሽያጭ ደግሞ ሁለት በመቶ ክፍያ ይቀበላሉ። አሻሻጮች የሚቀበሉት ይህ ክፍያ በእፎይፕላስ ቴክኖሎጂ የአገልግሎት ክፍያ (Service Fee) የሚባል ሲሆን የሽያጭ ክፍያውም ከአንድ በመቶ በታች ነው።

ለእያንዳንዱ ቤት የሚጠየቀው የክፍያ መጠን እንደቤቱ ዓይነትና እንደገዢው/ሻጩ ፍላጎት የሚወሰን ቢሆንም ሁሉም ክፍያዎች ከአንድ በመቶ በታች ናቸው። ግዢና ሽያጭ የሚከናወንባቸው ቤቶች የንግድ አልያም የመኖሪያ (Residential Houses) ሊሆኑ ይችላሉ። የመኖሪያ ቤቶችም ደግሞ የቅንጦት (Luxury) አልያም የጋራ መኖሪያ (Condominium) ሊሆኑ ይችላሉ። የአገልግሎት ክፍያ የሚጠየቀው በአገልግሎት ፈላጊው ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ነው። አብዛኛው የመኖሪያ ቤት ፈላጊ ኅብረተሰብ መደገፍ ያለበት ስለሆነ አገልግሎቱ በነፃ የሚሰጥ ይሆናል። ሻጩ ለድረ ገፁ ለሚያቀርበው የቤቱ መረጃዎች ድርጅቱ ክፍያ አይጠይቅም። ሽያጭ በሚፈፅምበት ወቅት አሁን ከሚከፈለው ሩብ እንኳ የማይሆን የአገልግሎት ክፍያ ይቀበላል። በዚህም ገዢና ሻጭ እስከ 200ሺ ብር ያተርፋሉ።

ቴክኖሎጂው የሚጠቀማቸው መተግበሪያዎች ቀላልና ሁሉም ሰው በሚረዳው መንገድ የተሠሩ ናቸው። በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው።

ቴክኖሎጂው ቀጥተኛ የሆነ የፋይናንስ ትስስር ለመፍጠርም ያስችላል። ቤት መግዛት የሚፈልግ ሰው ብድር ከፈለገ በዚሁ መተግበሪያ ላይ በቀጥታ የብድር ሂሳብ ቁጥር መክፈት ይችላል። ድርጅቱ የብድር ጥያቄውን ከድርጅቱ ጋር በትብብር ለመስራት ትስስር ለፈጠሩ ባንኮች ይልካል። ይህ ሁኔታ በተለይም ለዳያስፖራው ትልቅ ዕድል ይፈጥራል።

### ለአገራዊ ኢኮኖሚው የሚኖረው በጎ አስተዋፅኦ

እፎይፕላስ ቴክኖሎጂ ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት መሻሻል የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል። በዋናነት በቤት ግዥኛ ሽያጭ ዘርፍ እየታየ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ያስችላል። ቴክኖሎጂው ለቤት ግብይት መረጃ ትኩረት ይሰጣል። ግብይቱ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ደግሞ አላስፈላጊ የዋጋ ንረት ይቀንሳል። የግብይት ሂደቱም ፈጣን ይሆናል። የግብይት ሂደት ፈጣን ሲሆን የምጣኔ ሀብት እድገትም ይጨምራል። ለአጠቃላይ አገራዊ የዋጋ ንረት አስተዋፅኦ ካላቸው ነገሮች አንዱ በቤት ግብይት ዘርፍ ያለው የዋጋ መጨመር በመሆኑ በዚህ ዘርፍ ያለውን ዋጋ መቆጣጠር ለጠቅላላው የዋጋ ንረት ቅነሳ ሚና ይኖረዋል።

በቤት ግብይት ሂደት ውስጥ ከድርጅቱ ጋር በትብብር የሚሠሩ የመንግሥት ተቋማት (ከካርታ፣ ከውልና ማስረጃ፣ ከፍርድ ቤት ጋር የተገናኙ) አሉ። ይህ ትብብርም በግብይት ሂደት ውስጥ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመቀነስና ለመቆጣጠር ያስችላል።

ግብይቶች ሕጋዊ፣ ግልጽና ፍትሐዊ ሲሆኑ መንግሥት ከግብር የሚያገኘውን ጥቅም ያስከብራል። መንግሥት ከግብር የሚያገኘው ገቢ ለአገር ልማት የሚውል በመሆኑ በሂደቱ አገርና ሕዝብ ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪም በቀን፣ በወርና በዓመት የተመዘገበው የግብይት ብዛት በመነሳት ጥናቶችን የማካሄድ እቅድ ስላለ በቴክኖሎጂው የትግበራ ሂደት የሚገኙ ውጤቶች ለፖሊሲ ግብዓትነት የሚያገለግሉ ይሆናል ተብሎም ይታመናል።

### በትግበራው የተገኙ ውጤቶች

እፎይፕላስ የቴክኖሎጂ አገልግሎት ይፋ ከተደረገ በኋላ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ግብይት ለመፈፀምና አገልግሎቱን ለማግኘት ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦችና ተቋማት ቁጥራቸው በየቀኑ እየጨመረ ነው። ይህም ዳያስፖራው ኅብረተሰብ የውጭ ምንዛሬ ወደ አገሩ በመላክ ገንዘቡን ሀብት በማፍራት ላይ እንዲያውለው ያስችለዋል። ብዙ አሻሻጮችም (Agents) ከድርጅቱ ጋር አብረው ለመሥራት ፍላጎት አሳይተዋል።

እፎይፕላስ የተማከለ የመረጃ ቋት አደራጅቷል። ብዙ ሪል ስቴቶች (Real Estates) ከእፎይፕላስ (efoyplus.com) የመረጃ ቋት ጋር ትስስር ፈጥረዋል። በቀጣይም የቀሩት ሪል ስቴቶች ወደ ቴክኖሎጂው የመረጃ ቋት እንዲገቡ ይደረጋል። ድርጅቶቹ መረጃዎቻቸውን ወደ መረጃ ቋቱ ሲያስገቡ አማራጭ ቤቶቻቸውን፣ ከዚህ ቀደም ያላቸውን የአፈፃፀም ብቃት እንዲሁም ወደፊት ያሏቸውን የፕሮጀክት አማራጮች በተመለከተ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ ያቀርባሉ። በዚህም የኅብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግብይት እንዲኖር ምቹ ዕድል ይፈጠራል።

በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለውን አለመመጣጠን ለማስተካከል የቤት ገንቢዎች ድርሻ ወሳኝ በመሆኑ የእነርሱ በቴክኖሎጂው መታቀፍ ችግሩን ለማቃለል ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ገንቢዎች ስለድርጅታቸው ሥራዎች በቂ መረጃዎችን ስለማያቀርቡ ከኅብረተሰቡ ጋር በሚፈለገው መጠን ተገናኝተዋል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። እፎይፕላስ ገንቢዎች በቂ መረጃ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። የመረጃ ፍሰቱ ፈጣን ከሆነ ደግሞ ግብይትና የገንዘብ ፍሰቱም ፈጣን ይሆናል።

### ሌሎች አገልግሎቶችና እቅዶች

እፎይፕላስ በቤት ግብይት ዘርፍ የሚታዩ ችግሮች ቅድሚያ የሚሹ በመሆናቸው ቀዳሚ ትኩረቱን በዚህ ጉዳይ ላይ ቢያደርግም ከቤት ግብይት በተጨማሪ ሌሎች የዘርፉን ተግባራት የማከናወን እቅድም አለው። ከእነዚህ ተግባራት መካከል የሀብት አስተዳደር (Asset Management) ሥራ አንዱ ነው። ግብይት ከፈፀሙና ግንባታ ካከናወኑ በኋላ የሀብት አስተዳደር ሥራ እንዲከናወንላቸው ፍላጎት ላላቸው ግለሰቦችና ተቋማት አገልግሎቱን የመስጠት እቅድ አለው።

በቤት ግዥና ሽያጭ ዘርፍ ጥናቶችን በማካሄድ ለመንግሥት ፖሊሲ አውጪዎች ግብዓት ለማቅረብም ይሠራል። የገበያ ትስስር መፍጠርም ሌላው ተግባር ነው። የቤት ዋጋ ሊቀንስ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ የግንባታ ግብዓቶችን አቅራቢዎችንና ፈላጊዎችን በማገናኘት ነው። ለአሻሻጮች ስልጠና በመስጠት ባለሙያዎቹ ዘመናዊና ፍትሐዊ በሆነ ግብይት ውስጥ እንዲሳተፉና ጤናማ የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ለማድረግ ጥረት ያደርጋል።

የእፎይፕላስ ዋነኛው ፍላጎትና ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጣንና የሰለጠነ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ነው። ለዚህ ደግሞ የተቀናጀ የመረጃ ሥርዓት ያስፈልጋል። የእፎይፕላስ ቴክኖሎጂ መነሻም ይኸው ነው። ድርጅቱ በአሁኑ ጊዜ ለ25 ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን በቀጣይ ጊዜያት በሚያከናውናቸው የማስፋፊያ ተግባራት ደግሞ እስከ 200 ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅዷል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## አሉታዊ ትርክትን በወንድማማችነት ትርክት የመለወጥ መልካም ጅማሮ

**አስቴር ኤልያስ**

> **እያንዳንዱ ዜጋ የወንድማማችነትንና የእህትማማችነትን ትርክት የሚያቀነቅን ከሆነ በየቦታው በጽንፈኝነት ምክንያት እየተፈጠረ ያለው የመገፋፋትና የመፈናቀል ፈተና በሙሉ ይቆማል**

በኢትዮጵያ የነበሩ አሉታዊ ትርክቶችን በወንድማማችነትና እህትማማችነት መንፈስ በመለወጥ ወደፊት የማስቀጠል ጉዞ ተጀምሯል። ለዚህም ባለፉት አራት ዓመታት ውድቀቷን የሚመኙ አካላት እንደሚያስቡት የምትበታተን አገር እንዳልሆነች የሚያመላክት ወሳኝ ጥንስስ ተጥሏል። ይህንንም ማስቀጠል የሚችሉ ተቋማትም ሆኑ ሌሎች መልካም ጅምሮች እየታዩ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ዜጎቿ ቁርጠኞች ሊሆኑ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው ‹‹ስለኢትዮጵያ›› በተሰኘው መድረክ ላይ ተወስቷል።

በሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ እንደሚሉት፤ የትርክት ለውጥ ተጀምሯል ሲባል ከለውጡ በፊት በኢትዮጵያ የነበረው አሉታዊ ትርክት በመልካም ትርክት እየተለወጠ መምጣቱን የሚያሳዩ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን የሚያሳይ ነው። የቀደመውን ክፉ ትርክት መለወጥ የሚያስችሉ መንገዶች ተጀምረዋል ሲባልም በዋናነት የትርክት ለውጡ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾችና እህትማማቾች ናቸው የሚል ነው። ይህም ኢትዮጵያውያኑ በባዕድነትና በመጤነት የሚተያዩ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ሲሆን፣ ይህ የትርክት ለውጥ ኢትዮጵያን ለማስቀደም ትልቅ መሠረት የሚጥል ነው።

አሉታዊ ትርክት ናቸው ከሚባሉት መካከል የጥላቻ፣ የቂም በቀል፣ የመከፋፈል ትርክት ሲሆን፣ እነዚህን በወንድማማችነት ትርክት ለመተካት የሚያስችል መልካም ጅማሮ መኖሩን ዶክተር ቢቂላ ያብራራሉ። በሌላ በኩል ዜጎች እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩና እንደባይተዋር እንዲተያዩ የሚያደርገው ትርክት ተጠቃሽ ሲሆን፣ ሰው የትም ስፍራ ይወለድ ወይም ይኑር ወንድማማች ነውና አብሮ ይኖራል የሚለውን ትርክት የመትከል ጅማሮ ነው የተጀመረው ሲሉ ያስረዳሉ። ነገር ግን ይህን ማስቀጠል የሚችልና በኢትዮጵያ ውስጥ ባህል ሊሆን የሚችል ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ በመጥቀስ፤ ይህም የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ትርክት ማለት እንደሆነ ያብራራሉ። ባለፉት አራት ዓመታት የአብሮነትና አብሮ የመቀጠል ትርክት፣ አንዱ ሌላውን እንደ ዓይኑ ብሌን የማየት ትርክት፣ እንደመጤ ያለመተያየት ትርክት የተተከለበት ጊዜ ነበር ያሉት ዶክተሩ፣ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዜጋ ከየትም ይምጣ ከየት ወንድምህ ነው የሚል ትርክት ለመሥራት ተሞክሯልም ይላሉ።

ተጀምሯል ከተባለው ትርክት ውስጥ ዋና ዋና የሚባሉ ጉዳዮችም ተመዝግበዋል፤ ከእነዚህም አንዱ የተቋማት ግንባታ ሲሆን፣ ይህም መልካም የሚባል ጅማሮ ነው። ተቋማትን መገንባት ካልቻልን ኢትዮጵያን ማስቀጠል አንችልም የሚል ትልቅ ቁርጠኝነት በኢትዮጵያ ተጀምሯል። ለአብነት ያህል የፍትህ፣ የዴሞክራሲ፣ የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ፣ የጸጥታና ደህንነት በጥቅሉ ለመጪው ትውልድ የሚበጁ ተቋማትን መገንባት ተጀምሯል። የዴሞክራሲ፣ የደህንነት፣ እንዲሁም የፍትህ ተቋማት መልካም ጅምር ላይ መሆናቸውን ማስተዋል ይቻላል፤ ይህን የአሁኑ ትውልድ በአግባቡ ከሠራና ለሚቀጥለው ትውልድ ማስረከብ ከቻለ ነፃ፣ ገለልተኛና ዴሞክራሲያዊ ተቋም በመኖሩ አገሪቱን ማስቀጠል ያስችላል።

ይህ ብቻ አይደለም የሚሉት ዶክተር ቢቂላ፣ አካታች ህብረ ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ለመገንባት የሚያስችል ሁሉንም ያቀፈ፣ ሁሉንም ኃይማኖት፣ ብሔርና ቋንቋ የያዘ፣ በየትኛውም ማዕዘን ያሉ ዜጎችን ያቀፈና ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል መልካም እንቅስቃሴ ተጀምሯል ይላሉ። ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር ናት፤ እርሷን እንገነባለን የሚለው ጅማሮ የተጀመረበት ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ተፈጥሯል ሲሉም ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ የዋጋ ሁኔታና የኑሮ ወድነት የሚፈታተነን ቢሆንም ኢኮኖሚውን ከውድቀት ለመታደግ የሚያስችሉ ጠንካራ ውሳኔዎች እየተወሰኑ ናቸው ማለት ይቻላል፤ ከለውጡ በፊት የአንድ ወር ደመወዝ መክፈል አቅቶት ሲንገዳገድ የነበረ ኢኮኖሚ እንዲያንሰራራ ለማድረግ የተቻለበት፣ በውጭ ጫና ምክንያት መድኃኒት ማስመጣት እንዲሁም ብድሩን መክፈል የማይችል ኢኮኖሚ የነበረውን ሁኔታ እንዲያገግም ማድረግ የተቻለበት፣ አፋጣኝ የኢኮኖሚ ሪፎርሞች የተቀየሰበትና የአገር ኢኮኖሚ ከወድቀት መታደግ የተቻለበት ወቅት ነበር ብሎ መናገር ይቻላል።

ኢትዮጵያውያን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓታቸው ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ምርጫ ማካሄድም ሆነ የአገር ህልውናና ሉዓላዊነት ማስከበር አይችሉም ተብሎ የተነገረ ቢሆንም ዴሞክራሲያዊ ምርጫና ሉዓላዊነትን ማስከበር የተቻለበት ወቅት መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አለመሆኑም እውን ነው። በተለይም አገር በተወረረበት ወቅት ኢትዮጵያውያን በተለያየ ግንባር በመሆን አገሪቱን ከውደቀት ያዳኑበት ዓመት መሆኑን በሚገባ መናገር ይቻላል። ይህ ሊመጣ የቻለው የወንድማማችነት ትርክት ቦታውን እየያዘ በመምጣቱ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ የፕሮጀክቶቻችንን አፈጻጸም በምናስተውልበት ጊዜ ሜጋ ፕሮጀክቶቻችን አያልቁም፤ ትውልድም ኢኮኖሚም የሚበሉ ናቸው በተባለበት ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ለአገልግሎት የበቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከዚህ መካከል ደግሞ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በብዙ አገሮች ዘመቻ የተካሄደበት ቢሆንም በፈተና ውስጥ ሆነንም ቢሆን ኃይል ማመንጨት እንደሚችልና የኢትዮጵያን ፍላጎት ማሳካት የሚችል ፕሮጀክት መሆኑን ያሳየንበት ወቅት መሆኑን መረዳት ይገባል ይላሉ።

ዛሬ ወንድማማችነት ያልነውን ትርክት የዛሬ ሃያና ሰላሳ ዓመት የሚወለደውም ልጅ ይህንኑ ወንድማማችነት የሚለውን ትርክት ሊያስተጋባ ይገባል። ወንድማማችነት ከዚህ በኋላ ወደኋላ የሚመለስ ነገር ሳይሆን ትውልድ እየተቀባበለ የሚያስቀጥለው መሆን አለበት። እንደ አገር የተቀመጠው ግብ የበለጸገች አገርን መገንባት ሲሆን፣ ይህ የአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያ ነው ብለዋል።

የጥላቻ ትርክትን በወንድማማችነትና በእህትማማችነት ትርክት የመለወጡ ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ የሚሉት ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር ዮሐንስ ረጋሳ ናቸው። ለውጡ ውስጥ እንደነበረና ለለውጡም አዎንታዊ ሚና እንደተጫወተ ሰው በአገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች መኖራቸው እሙን ነው። በዚህ ውስጥ ምንም እንኳ ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ ኢህአዴግ ማህበራዊው ነገር ላይ የተሻለ መስሎ ቢታይም ፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን ባለማስነካት በኩል አምባገነንነቱን ቁልጭ አድርጎ ሲያሳይ እንደነበር ዶክተሩ ይናገራሉ።

በኢኮኖሚው በኩል የአንድ ብሔር ገናናነት ሲንጸባረቅ ነበር ሲሉ የተናገሩት ዶክተር ዮሐንስ፣ እንደማሳያ በኢኮኖሚው በኩል ሌላው ብሔር የበይ ተመልካች ሆኖ መክረሙን ይጠቅሳሉ። ለአብነትም በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ ብቻ ቢወሰድ እንኳ ከአንድ እስከ አስር ያለው ደረጃ የተያዘው በአንድ ብሔር መሆኑን ያመለክታሉ። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ተጠቃሚ መሆን ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ የሚለውን ትርክት ነው። ይህ ደግሞ አንዱን ልጅ ሌላውን የእንጀራ ልጅነት ስሜት እንዲሰማው ከማድረጉም በላይ የበይ ተመልካች ላለመሆን አመጽ እንዲቀጣጠልና ለውጥ እንዲመጣ ማስቻሉንና የለውጡ መንግሥት መመስረቱን ይናገራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ገደማ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ራሱን እንደ ኢትዮጵያዊ እንዳያይ ሲሰበክ ቆይቷል። ለአብነት ያህል ደርግን ከእኛ ጋር ታግለው አልጣሉም በሚል ውሃ በማያቋጥር ምክንያት ብቻ ጥቂት የማይባሉ ክልሎች በአጋርነት ሲፈረጁ ቆይተዋል። ይህን ከፋፋይ ትርክት ለመጣል ትውልዱ ጥያቄ በማንሳት መሞገቱ ይታወቃል። ሲነገሩ የነበሩ አሉታዊ ትርክቶች ብዙውን ጊዜ ነጥሎ አንዱን የማጥቂያ መሣሪያ ሆነውም ከርመዋል።

እኔ ነኝ የበላይ ከሚለው ትርክት ውስጥ አንዱ ማሳያ በወቅቱ የነበረው መከላከያ የአገር አለኝታ መሆን ሲገባው መሣሪያ ታጣቂም ኢንቨስተርም የሆነበት ዘመን ነበር። ለዚህ ደግሞ ሲነገር የነበረው ትርክት እኔ ነኝ ደርግን የጣልኩት፤ እኔ ነኝ ለዚህች አገር ያለሁት የሚል ነው። ከዚህ የተነሳ በመከላከያ ውስጥ ብዝሃነትን ያስተናገደ ማንነት አልነበረም። አድራጊ ፈጣሪ አንደኛው ወገን ብቻ በመሆኑ በሌላው ዘንድ የባይተዋርነት ስሜት ተፈጥሮ ቆይቷል። ይህ ጥላቻና ቂምን አዝሎ ዜጋው ለሌላ ትግል እንዲሰናዳ ሲገፋፋውም ከርሟል።

ዜጋው፣ ኢኮኖሚውና ፖለቲካው አይመለከትህም፤ ለዚያ የሚሆን ችሎታ የለህም፤ አንተ ማድረግ ያለብህ ባህልህን ቋንቋህን መናገር ነው፤ ስለተባለ ብቻ ተገፍቶ መዝለቅ አልሆነለትም። ስለዚህም ሲደርስበት የነበረውን አሉታዊ ትርክት በመጣል ነፃነቱን ማወጅ በመፈለጉ ለውጡ ሊመጣ ችሏል ብለዋል።

የመናናቅ መንፈስ ነበር የሚሉት ዶክተር ዮሐንስ፣ አንዱ ሌላውን ይንቅ ነበር፤ ይህ ክፉ ትርክት ነው በማለት ይገልጻሉ። የእንትና ቋንቋ ከእንትና የተሻለ ነው ብሎ አሉታዊ ትርክትን ከማራመድ ይልቅ የእገሌንም የእገሌንም ቋንቋ ባውቅ እኔ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ አልሆንም ወደሚለው አዎንታዊ ትርክት መምጣት ይጠበቅብናል ይላሉ። ቋንቋ አወቅን ማለት በየትኛውም ስፍራ ተገኝቶ መሥራትም መነገድም ይቻላል፤ በዚህ ውስጥ ደግሞ መጠቀምም ማትረፍም ይመጣል። ስለሆነም መናናቅን ወደመከባበር መለወጥ ይጠበቅብናል ሲሉ ያስረዳሉ። በእርግጥ በቋንቋ ማሳደግ በኩል አዎንታዊ ሚና ኖሮ ቢቆይም በተዘዋዋሪ ግን የእኔ አውቅልሃለሁ ትርክት በመኖሩ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ዘርፍ እኩል ተጠቃሚ መሆን አለመቻሉን ነው የሚናገሩት።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት እየታዩ ያሉ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ አካሄዶች መጥቀስ ይቻላል። ለአብነትም በለውጡ መንግሥት የተመለሱ ጥያቄዎች መኖራቸው አንዱ ተጠቃሽ ጉዳይ ነው። ለዚህም እንደማሳያ ሊጠቀስ የሚችለው አስረኛና አስራአንደኛ ክልሎች መመስረት መቻላቸው ነው። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ የእኔም ናት ወደሚለው መልካም የሆነ ትርክት የሚያመጣ ነው። በዚህም አብሮነት ይዳብራል፤ ይጎለብታልም።

በኢትዮጵያውያን መካከል ኢትዮጵያዊነት እንዲዳብር በለውጡ መንግሥት ከተሠሩ ሥራዎች ለማስታወስ ያህል ቀደም ሲል በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት አንድ ዶላር ከአንድ ማኪያቶ ለተሰኘው ፕሮጀክት የተሰጠው በጎ ምላሽ ነው ሲሉ ተናግረው፤ በዚህም መከፋፈል ስለሌለበት አንድነት ገኖ እንዲወጣ ማስቻሉን አስረድተዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው ገበታ ለአገር መርሃግብር ቀደም ሲል ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ አዘንብሎ የነበረውን የቱሪስት መስህብ ወደሁሉም እንዲሆን ማድረግ የሚያስችል ስለመሆኑ ነው የሚያስረዱት። ለፕሮጀክቶቹ ኢትዮጵያውያን በእኩል ስሜት ማዋጣት እንዲችሉ መደረጋቸውም የጋራ መንፈስ እንዲፈጠር ያስቻለ ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ የተገነቡ እንደ እንጦጦ፣ አንድነት እንዲሁም ወዳጅነት ዓይነት ፓርኮችን ስናስተውል ከስማቸው ጀምሮ የሚተርኩት ኅብረትንና አብሮነትን ነው። ፓርኮቹ የሕዝብ ናቸው። በጥቅሉ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው እነእገሌ እንጂ እኛ አልተጠቀምንም የሚለው አስተሳሰብ በተግባር ተቀይሮ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸውና ይህ ይጎልብት የሚል አተያይ ነው ያለኝ ብለዋል።

ሌላው ደግሞ መደመር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በራሱ መልካም የሆነ ትርክትን ያዘለ በመሆኑ ለዜጎች ኃይልን የሚጨምር ነው። እንዲያውም መደመር የሚለው ሃሳብ ላለፉት ጊዜያት ተነጣጥሎና ተገፋፍቶ የነበረውን ማኅበረሰብ በወንድማማችነት መንፈስ በመደመር ጉልበት ማግኘት የሚያስችል መንገድ ነው ብለዋል።

ዶክተር ቢቂላ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ አሁን የተደረሰበት አዎንታዊ ትርክት እንዳይንሸራተት ከማድረጊያ መንገዶች አንዱ ከሁሉም ቀድሞ መሠራት ያለበትና ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያለ ልዩነት መረባረብ ያለበት የወንድማማችነትንና የእህትማማችነትን ትርክትን ማጽናት ላይ ነው። ወንድማማችነትና እህትማማችነት ጸንቷል ማለት የሚቻለው ደግሞ ከሰሜን የመጣው ደቡብ ላይ እንዲሁም ከምዕራቡ የመጣው ምሥራቅ ላይ መኖርና መሥራት ሲችል ነው። የትርክት ለውጡ የትም ተወለድ የትም እደግ ኢትዮጵያዊ እስከሆንክ ድረስ ወንድሜ ነህ የሚለውን ትርክት መርህ ማስያዝ ነው። በዚህ መልኩ ወንድም ወንድሙን እንደ ዓይኑ ብሌን መጠበቅ ካልቻለ አገርን ማስቀጠል አንችልም። በብዝሃነት አንዱ ሌላውን አቅም እንዲሆን ማስቻል ነው። እያንዳንዱ ዜጋ የወንድማማችነትንና የእህትማማችነትን ትርክት የሚያቀነቅን ከሆነ በየቦታው በጽንፈኝነት ምክንያት እየተፈጠረ ያለው የመገፋፋትና የመፈናቀል ፈተና በሙሉ ይቆማል። የጥላቻና የቂም በቀል ትርክ የሚቀጥል ከሆነ ግን አገርን ማስቀጠል ቀርቶ ባለችበት ማቆየት አይሞከርም።

የተዘራውን የጥላቻ ትርክት በመንቀል ብዝሃነትን ያስተናገደ ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት መትከል ይጠበቅብናል የሚለው ትልቁ ሥራ ነው የሚሉት ዶክተር ቢቂላ፣ በተመሳሳይ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ ከፍተኛ ሥራ ሊሠራ ይገባልም ብለዋል። ይህ ደግሞ እንደ ዜጋ የሁሉም ኢትዮጵያ ድርሻ ነው የሚለው ላይ ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ የግድ መሆኑንም አስምረውበታል።

ጽንፈኝነትና አክራሪነት ፈተና ነው፤ የእኔ ብሔር፣ ኃይማኖት፣ ማንነት ብቻ ይኖር፤ የሌሎቻችሁ በሙሉ ይጥፉ ማለት የዜጎችን ደህንነት ፈተና ውስጥ የሚያስገባ ስለሆነ መጋፈጥ ይጠበቅብናል። ምክንያቱም ወንድማማችነትና አንድነት በጠፉ ጊዜ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያዊነትን ለማፍረስ ይሞክራሉ፤ ስለዚህ ጽንፈኝነትንና አክራሪነትን የማይሸከም ማኅበረሰብ መፍጠር ትልቁ የቤት ሥራ ነው። ጽንፈኝነትንና አክራሪነትን መጸየፍና ማጋለጥ ደግሞ የዜጎች ድርሻ ነው ብለዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የሴት ተማሪዎችን መጠነ ማቋረጥ ለመቀነስ የንጽሕና መጠበቂያዎችን በግዢ ሥርዓት ማካተት

ሰላማዊት ውቤ

ሴት ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታ ከሚያስቀሩ ምክንያቶች አንዱ የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ እጦት ነው። በቅርብ ዓመታት በዚሁ ዙርያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ካሉ ሴቶች 22 ሚሊዮን የሚሆኑት የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ አያገኙም።

ችግሩ በአፍሪካ በተለይም በእኛ አገር ይጉላ እንጂ በአውሮፓና በምራባውያኑ ሴቶች ዘንድ መኖሩን ጥናቶች ይጠቁማሉ። ለአብነት በዩናይትድ ኪንግደም ከሚገኙ ሴቶች መካከል 10 በመቶው የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ የመግዛት አቅም እንደሌላቸው ጥናቶች ይጠቁማሉ። ከነዚሁ ሴቶች ውስጥ 15 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች አቅም የንፅሕና መጠበቂያውን መግዛት የሚችል ቢሆንም በበቂ ሁኔታ የሚያስገዛ እንዳልሆነ ጥናቱ ያመላክታል። ጭራሹኑም 19 በመቶው በዋጋ ውድነት ምክንያት ጥራት የሌላቸውንና የማይመቹ የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያዎችን እንደሚጠቀሙም በጥናቱ ተጠቅሷል። ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 21 ዓመት ከሆኑ ሴቶች መካከል 71 በመቶ የወር አበባ መገልገያዎችን ከየመድኃኒት ቤቶችና መደብሮች ለመግዛት የሚሸማቀቁና የሚፈሩበት ሁኔታም መኖሩ በጥናቱ ተመላክቷል።

ወደ እኛ አገር ስንመጣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ያዘጋጀውን አንድ ጥናት ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት ግንዛቤ እንደሌላቸው፣ ሲመጣባቸው እንደሚያፍሩ፣ ንጽህና መጠበቂያውን መግዣ አቅም እንደሌላቸው በዚህ ምክንያትም አብዝተው ከትምህርት ገበታቸው እንደሚቀሩና እንደሚያቋርጡ አመላክቷል። የዛሬ ጽሑፋችንም በዚሁ ዙርያ ያተኮረና በመድረኩ የተገኙ የእቴጌ መነን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎችን ተሞክሮ ያካተተ ነው።

ተማሪዎቹ ትምህርት ቤታቸው እያንዳንዱ 10 ፍሬ የሚይዝ በወር ሁለት እሽግ የንጽህና መጠበቂያ (ፓድ) እንደሚሰጣቸውና እጥረት እንደማያጋጥማቸው ይናገራሉ። ሁሉም ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች እንዲህ እንደነሱ ትምህርት ቤት የንጽሕና መጠበቂያ መስጠትና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ መሥራት እንዳለበትም ገልፀዋል።

ተማሪ ሀዊ ሰብስቤ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ ያየችው በ13 ዓመቷ ሲሆን ያኔ ሰባተኛ ክፍል ነበረች። የቤተሰቡ የበኩር ልጅ እሷ በመሆኗ ቀደም ብላ ስለ ወር አበባም ሆነ በዚሁ ወቅት መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄዎች የምታውቀው ምንም ነገር አልነበረም። በዚህ ጉዳይ ከእናቷ ጋርም አውርታ አታውቅም። ከመምጣቱ በፊት ራሷን እያመማትና ሆዷን እየቆረጣት ነበር። መኝታ ክፍሏ ውስጥ ተኝታ ነው ድንገት የመጣባት። አንሶላዋ በደም ተነክሮ ስታየው ደነገጠች። ዘላ ከአልጋዋ ላይ ስትወርድ በእግሯ ደም ሲወርድ እግሯ የተቆረጠ ሁሉ መሰላት። ፈሳሹ የሚወጣው ከእግሯ አለመሆኑን ስታይ እፍረት ተሰማት። በዚህ መካከል ወደ መኝታ ክፍሏ ከመጣችው እናቷ ለመደበቅም ሞከረች። ሆኖም እናቷ የሆነችውን በግልፅ በማየቷ ነገረቻትና ስለ ሁኔታው ተረዳች። እናቷ ለአባቷ ነገረችውናም አባትና እናቷ በቃ ልጃችን አደገች ትልቅ ሰው ሆንሽልን ብለው በማሳሳቅ የወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያና ቁሳቁሶችን እንዲሁም ሊያስፈልጋት ይችላል ብለው ያሰቡትን ሁሉ ገዝተው ሰጧት።

ከዚህ በኋላ በአምስት ዓመት ዕድሜ የምትበልጣት ጓደኛዋ እንደነገረቻት በቤተሰቧ ውስጥ ግልፅነት ባለመኖሩና በመፍራቷ እስከ አሁን ለወላጆቿም ሆነ ለእህቷና ወንድሞቿ የወር አበባ እያየች መሆኗን አልተናገረችም። ንጽህና መጠበቂያው የሚታደልበት ትምህርት ቤት ከመግባቷ በፊት የነበረችበት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እያለች ትጠቀም የነበረው በነጠላና በተለያየ አሮጌ ጨርቅ ነበር። ይሄ ደግሞ በአካሏ ላይ ጉዳት ያስከትል እንደነበር ትናገራለች። ቤተሰቦቿ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው በመሆናቸው እሱንም እንደልብ ስለማታገኝ እያጠበች መጠቀም ግድ ይላታል። ቤት ውስጥ አጥባ እንዳታሰጣው ስለሚታይባት እርጥቡን አድርጋው ትመጣና ስትቀመጥ እርጥበቱ ቀሚሷን የሚያበላሽበት ሁኔታ እንደነበር አውግታለች።

ተማሪ ዮስቲና ተጋረድ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየችው የሰባተኛ ክፍል ትምህርቷን ልታገባድድ ሁለት ወራቶች ሲቀራት ነው። የመጣባት በአጋጣሚ ቤት ውስጥ ሆና ስለነበር ፈጥና ለእናቷ ነው የነገረቻት። ተማሪዋ እንደገለፀችልን ታላቅ እህቷን ታይ ስለነበር በአየችበት ወቅት ትልቅ የሆነች ሆኖ ስለተሰማት ደስ ብሏት ነው የነገረቻት። አሁንም ቢሆን ውጪ ገጥሟት አያውቅም።

ነገር ግን የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ በነበረችበት ጊዜ ትምህርት ቤት እያሉ የሚመጣባቸው ሴት ተማሪዎች ታውቃለች። ልብሳቸው በፈሳሹ የተበላሸባቸውም ገጥሚታል። ሴት ተማሪዎች ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ሲገጥማቸው ያፍራሉ። በአንዳንድ ትምህርት ቤት በዚህ ዓይነት ወቅት ለተማሪ የሚሰጥ የንጽሕና መጠበቂ ቢኖርም ደፍረው አይጠይቁም። ሆኖም ወደ ቤታቸው ሄደው ልብስ ቀይረውና ታጥበው ይመጣሉ። በተለይ ልብሷን የነካው ከሆነ ስለሚያፍሩ ሳይነግሯት እንዳላየ ሆነውም ያልፋሉ። ኮታቸውን ወይም ሹራባቸውን አውልቀው እንድትሸፍንበት የሚሰጡ ወንድ ተማሪዎችም አሉ። ፈሳሹ የሚበዛባቸው መውጫ ቀኑ የሚረዝምባቸው ተማሪዎች እጅግ ሲቸገሩ አስተውላለች። ለነዚህ ዓይነት ተማሪዎች ምን አልባት አሁን ላይ በትምህርት ቤታቸው አማካኝነት በወር የሚሰጠው ሁለት እሽግ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ላይበቃቸው ይችላል።



ተማሪ አናቶል መርድ



ተማሪ ሀዊ ሰብስቤ



ተማሪ ዮስቲና ተጋረድ



ፎቶ፡ በሰላማዊት ውቤ

አቶ መለሰ ድንቁ

ከዚህ በፊት የምትማርበት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪም ሆና የሚታጠበው ይሰጥ ስለነበር እሷ በወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ በኩል ተቸግራ አታውቅም ።

የእቴጌ መነን የሁለተኛ ደረጃ አዳሪ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ አናቶል መርድ 17 ዓመቷ ነው። አናቶል የወር አበባ ማየት የጀመረችው በ14 ዓመቷ ነው። ሁለት ታላላቅ እህቶች አሏት። እህቶቿ ቀደም ሲል ስለ ወር አበባ ይነግሯት ነበርና ጥሩ ግንዛቤ ነበራት። በተለይ እሷ የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ ባየችበት ወቅት 10ኛ ክፍል የነበረችው እህቷ ብዙ ሴት ተማሪዎች በወር አበባ ወቅት ንጽሕና መጠበቂያ በማጣት እንደሚቸገሩ አንዳንዶቹም ቀድሞ ግንዛቤው እንደሌላቸውና እሷም የነዚህ ተማሪዎች ዕጣ እንዳይገጥማት በዚህ ላይ ከስድስተኛ ክፍል ጀምሮ ስለ ወር አበባ ታሳውቃት ነበር። ቀደም ብላ ከእህቶቿ በመስማቷ ግንዛቤ ቢኖራትም ብዙ ጓደኞቿ እውቀቱ አልነበራቸውም። ግንዛቤውን ይይዙ የነበረው ግራ ተጋብተው እንደነበርም ታስታውሳለች። ብዙዎቹም ትምህርቱን ይከታተሉ የነበረው በእፍረት ተሸብበው ፊታቸው ላይ ላብ ቸፈ እያለ ሳይቀር መሆኑም ትዝ ይላታል። እነዚህ የጾታ አጋሮቿ ስለ ወር አበባ ቀደም ብለው ግንዛቤ ያላቸው ሲሆኑ እሷም ትምህርቱን በምትከታተልበት ወቅት ተመሳሳይ ስሜት እንደነበራት አትዘነጋውም። በዚህ ትምህርት ሰዓት ወንድ ተማሪዎች በፊናቸው ይስቁና ያላግጡ የነበረበትንም ሁኔታ ታዝባለች። ያም ሆነ ይህ የአገራችን ኢትዮጵያ ዋና መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚኖሩና የተወለዱ ሴት ተማሪዎች ስለ ወር አበባ እንደ እሷ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ለመሆናቸው በተለያየ ምክንያት ከተለያዩ የገጠር አካባቢዎች መጥተው ከነሱ ጋር በመጀመሪያ ደረጃ የመንግሥት ትምህርት ቤት በአንድ ክፍል ሲማሩ ከነበሩ ሴት ተማሪዎች ጋር በማነፃፀር ማየት ችላለች።

በተዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ ያገኘናትና ተሞክሮዋን ያካፈለችን አደራ ባርክልኝ ተወልዳ ያደገችው በአማራ ክልል ምሥራቅ ጎጃም ዞን መርጦ ለማርያም የምትባል የገጠር ከተማ ውስጥ ነው። አደራ እንደነገረችን የወር አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ የታያት ደብል ደብል መታ በ14 ዓመቷ የደረሰችበት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ሳለች ነበር። «ስለ ወር አበባ ቀደም ብሎ ምንም ዓይነት ግንዛቤ አልነበረኝም ብል ይሻላል» ስትል ትውስታዋን ትጀምራለች። ምክንያቱም እሷ ተወልዳ ባደገችበት አካባቢ ስለ ወር አበባ ከወላጅ ጋር ማውራት ነውርና እጅግ አሳፋሪ ነው። ሌላው ቀርቶ አዋቂ ልጅ ፊት አያወራም። ያወራ ልጅ ቢገኝ አዋቂ ሲያወራ ማዳመጥ ልጅን እንደባለጌ ስለሚያስቆጥረው ይገሰጽና ይባረራል። ሰባተኛ ክፍል ሆና በተወሰነ መልኩ የተማረችውም ቢሆን አስተማሪውም ሆነ ተማሪው ነውረኛ ጉዳይ አድርጎ ስለሚቆጥረው ነካ ነካ አድርጎ የማስተማርና ከልብ ያለማዳመጥ ሁኔታ በመኖሩ ተዘንግቷታል። እንደምታስታውሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣባት ክፍል ውስጥ በትምህርት ላይ ሳለች ነበር። ሞቃትና ፈሳሽ ነገር ሲሰማት ክፉኛ ደንግጣለች። እራሷን እንደምንም አረጋግታ ፈሳሹ ምን ሊሆን እንደሚችል ስታስብ ራሷን ስታ ሽንቷን የለቀቀችው መሰላት። ሆኖም ፈሳሹ ሲጨምር ያለ ውስጥ ሱሪ የለበሰችውን የውስጥ ልብስ አልፎ ወደ ቀሚሷ መዝለቁን ስታስተውል ድንጋጤው ወደ ብርክ ተለውጦ መንቀጥቀጥ ጀመረች። «ስለ ክብረ ንጽሕናም ሆነ ስለ ወር አበባ ባላውቅም ክብረ ንጽሕናየን ያጣሁ ሁሉ መስሎኝ ነበር» አደራ በዚህ ምክንያት የክፍሉ ተማሪ አይደለም የትምህርት ቤቱ ተማሪ ወጥቶ እስከሚያልቅና በወር አበባ ፈሳሽ የረጠበው ቀሚሷ ከወንበሩ ጋር እስኪጣበቅ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ አልተነሳችም። ሰርክ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ከትምህርት ቤት ወደ ቤት አብራት ለምትሄደውና ከአጠገቧ ለምትቀመጠው ጓደኛዋ እንኳን የሆነችውን አልነገረቻትም። እንዲያውም ከወንበሬ ከተነሳሁ የሆንኩትን ታይብኛለች በሚል እጅግ ፈርታና ተሸማቅቃ ነበር። ምን እንደሆነችና ለምን ከተቀመጠችበት እንደማትነሳና ወደ ቤት እንደማይሄዱ በጥያቄ ስትወተውታት ቆይታ ምላሽ ስታጣ ያመማት ስለመሰላት ወደ ቤቷ ሄዳለች። አደራ ሹራቧን አውልቃ ፈሳሽ የነካው ቀሚሷ ላይ በማሸረጥ ወደ ቤቷ ብትሄድም የሆነችውን ለቤተሰቦቿ ለመንገር አልደፈረችም። የወር አበባዋ መፍሰሱን እስኪያቆም ትምህርት ቤት አልሄደችም። አመመኝ በማለት ጓዳ ውስጥ ተደብቃ ነው የሰነበተችው።

በአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክተርና የጥናት ቡድኑ ሰብሳቢ አቶ መለሰ ድንቁ ያቀረቡትን ጥናት ዋቢ አድርገው እንደገለፁት በወር አበባ ንጽሕና መጠበቂያ እጦት ምክንያት በርካታ ሴቶች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። በራስ መተማመናቸው ይቀንሳል። ራሳቸውን የሚያገሉበትም ሁኔታ አለ። ትኩረት የሚሰጡት ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ለሚገጥማቸው ችግር እንጂ ለትምህርት ባለመሆኑ በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ይቀንሳል። ውጤታማም አይሆኑም። ትምህርት አቋርጠው ያለ አስተማሪ ፈቃድ ከክፍል ውስጥ ይወጣሉ። በአጠቃላይ በዚሁ በወር አበባ ምክንያት አንዲት ሴት ተማሪ በወር ከአንድ እስከ አራት ቀን ትቀራለች። ይሄ በዓመት ሲሰላ ከ22 እስከ 40 ቀን ይደርሳል። በመሆኑም ጥናቱ እነዚህንና ሌሎች ምክንያቶችን መሠረት አድርጎ ለሁሉም ለመንግሥት ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎች የወር አበባ ንፅሕና መጠበቂያ በጀት ተይዞለት መሰጠት አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። እንደሌሎቹ ሁሉ በግዢ ሥርዓቱ በጀት ሊያዝለት ይገባል ብለዋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**በሳምንታዊው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1960ዎቹ የታተሙ ጋዜጦችን ለዚህ ሳምንት ተመልክተናል። የጅብ መንጋ በሰዎችና በቤት እንስሳት ስላደረሰው ጉዳት፤ በሐረርጌ አሁን ሶማሌ ክልል በምንለው በደገሀቡር አካባቢ አንድ ነጋዴ በ20ሺህ ብር የውሃ ገንዳ ማሠራታቸውና ይህም በአካባቢው የሚከሰተውን የውሃ እጥረትና ድርቅ ለመከላከል እንደሚረዳ በወቅቱ መናገራቸውን፤ ከጎረቤቱ በግ ሰርቆ ያረደ ግለሰብ ተከሶ ስለመቀጣቱ የሚያትቱ በወቅቱ የተሰሩ ዘገባዎችን ከሃምሳ ዓመታት በላይ ወደ ኋላ ተመልሰን እንደሚከተለው ልናስታውስ ወደናል።**

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

### የጅብ መንጋ በረት ወርሮ ሰው ገደለ

ፍቼ፤(ኢ.ዜ.አ.) በሰላሌ አውራጃ በኩዩ ወረዳ በዳሮ ምክትል ወረዳ ውስጥ ኩዩ ከተባለው ቀበሌ ግንቦት ፰ ቀን የአቶ ሞቱማ ገሙን በበረት ውስጥ እንዳለ የወረረው የጅብ መንጋ አንድ ሰው ገድሎ ሲበላ በአምስት ሰዎች ላይ ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን የኩዩ ወረዳ ግዛት ፖሊስ ጣቢያ ገለጠ።

በጅብ መንጋ ተወርረው የነበሩት አቶ ሞቱማ ገሙን ለመርዳት ከጎረቤት በቅድሚያ ለርዳታ የደረሱትን አቶ ጀንቢ ሂርጄ የተባሉትን የ፵ ዓመት አዛውንት የጅብ መንጋ ወዲያውኑ አደጋ አድርሶባቸው ከገደላቸው በኋላ ከጭንቅላታቸውና ከእጃቸው በስተቀር የቀረውን ሰውነታቸውን በሙሉ ከስክሶ የበላቸው መሆኑን ሁኔታውን የተከታተሉት የ፲ አለቃ ገብረ ማርያም ፎራ አስረድተዋል።

ከዚህም በቀር ብዛቱ ከ፳ በላይ የሆነ የጅብ መንጋ ፈለቀች ሲሳይና ኃይሉ ቱሉ፤ ፈዬ ራፎ፤ ቱሉ ብሩና አቶ ሞቱማ ገሙን ነክሶአቸው በከባድ ሁኔታ ስላቆሰላቸው በገብረ ጉራቻ ክሊኒክ ተኝተው በሕክምና በመረዳት ላይ ይገኛሉ።

የአካባቢው ሕዝብ በማግስቱ ግንቦት ፱ ቀን ከጅብ መንጋ የተረፈውን የአቶ ጀንቢ ሂርጄን አስከሬን በቀበሌው ቤተ ክርስቲያን ቀብረው ሲመለሱ አንድ ጅብ ቀን ፲ ሰዓት ላይ በመንገድ ላይ አድፍጦ ከቀብር በሚመለሰው ሰው ላይ በድጋሚ አደጋ ለማድረስ ሲሞክር በጥይት ተመትቶ ሞቷል።

በዚሁ ጊዜ የጅቡ ሆድ ተቀድዶ ቢታይ ልዩ ምልክት ያለበት የሟቹ አስከሬን ከጅቡ ሆድ ውስጥ ተገኝቶ እንደነበር የክፍሉ ፖሊስ ጣቢያ በተጨማሪ አረጋግጧል።

የአገሬው ሕዝብ ይህን ከባድ አደጋ ያደረሰውን የጅብ መንጋ ለማጥፋት በማደን ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።ከኩዩ ፖሊስ ጣቢያ የደረሰን ሪፖርት እንደሚያመለክተው ግንቦት ፰ ቀን ለዘጠኝ አጥቢያ እኩለ ሌሊት ላይ ብዛታቸው ከአምስት የማይበልጡ ጅቦች የአቶ ሞቱማ ጋሙን የከብት በረት ሰብረው ከብቶቹን መብላት ጀመሩ።ከዚያም የከብቶቹ ባለቤት አቶ ሞቱማ ከብቶቻቸውን ለማስጣል የመከላከል ሙከራ ሲያደርጉ ጅቦቹ በመተባበር የአሁኑ ሰው ሁለት እጆቻቸውንና ታፋቸውን በመንከስ አቆሰሉዋቸው። ከዚያም ጅቦቹ በበረት ውስጥ የሚገኙትን ከብቶች በየተራ እየቦጨቁ በመጣል መብላት ቀጠሉ።በዚህም ሰዓት ሟቹ አቶ ጀንቢ ሄርጳና ሌሎችም ጐረቤቶች ሁኔታውን ሰምተው ለርዳታ ሲደርሱ እንደገና ፲፰ ጅቦች ከመጀመሪያዎቹ አምስት ጅቦች ጋር ሁነው ሰዎቹን ያለፍርሃት በመብላት በአንድ ሰው ላይ የሞት አደጋ ሲያደርሱ የቀሩት አምስት ሰዎች ላይ ከባድ የመቁሰል አደጋ ማድረሳቸውን ኩዩ ፖሊስ ጣቢያ አረጋግጧል። (ግንቦት 13 ቀን 1960 ዓ.ም አዲስ ዘመን)

### ነጋዴው በ፳ ሺህ ብር የውሃ ገንዳ ሠሩ

ጅጅጋ፤(ኢ.ዜ.አ.) በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በደገሀቡር አውራጃ በአዋሬ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ወልደዮሐንስ የተባሉ ነጋዴ በ፳ ሺ ብር ፳፫ ጫማ ስፋት ያለው አንድ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ አሠሩ።

አቶ ተስፋዬ ይህንን የማጠራቀሚያ ገንዳ ለማሠራት ያቀዱበት ምክንያት ሲያስረዱ፤በአዋሬ ከተማና በአካባቢው የውሃ እጥረት በመኖሩ አንዳንድ ጊዜ ድርቅ በሚሆንበት ወቅት አንድ በርሜል ውሃ ከ፲ ብር በላይ ስለሚሸጥ ይህንን የመሰለውን ችግር በኗሪዎቹ ላይ በመድረሱ ችግሩን ለመቋቋም ይረዳል ብዬ ነው ብለዋል።

ይህ አዲስ የተሠራው የማጠራቀሚያ ገንዳ ፩፻፫ ጫማ ርዝመት ፳፫ ጫማ ስፋት ፲፪ ተኩል ጫማ ጥልቀት ያለው ሲሆን ፤የማጠራቀሚያ ክፍል ደግሞ ፳ ጫማ ርዝመት ፳ ጫማ ስፋትና ፰ ጫማ ጥልቀት አለው። በዚሁ መሠረት ፲፯ ሺ ኪዩቢክ በርሜል ውሃ ለማጠራቀም የሚችል መሆኑ ታውቋል። (ግንቦት 13 ቀን 1960 አዲስ ዘመን)

### በ፩ በግ ስርቆት ዓመት ከስድስት ወር እስራት

ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ፡- ገብሬ አሻሜ የተባለው ሰው አንድ ዳለቻ ወጠጤ በግ ሰርቆ በማረዱ በመናገሻ አውራጃ ፍርድ ቤት ዓመት ከስድስት ወር እንዲታሰር ተፈርዶበታል።

ገብሬ ይህን ተግባር የፈጸመው በመናገሻ አውራጃ በአዲስ ዓለም በገነት ከተማ ሲሆን ፤በጉም አቶ ነጋሽ ማሞ የተባሉት ሰው ነው። ገብሬ ከአቶ ነጋሽ የሰረቀውን በግ ከቤቱ ወስዶ ሲያርድ የበጉ ድምጽ በመሰማቱ የበጉ ባለቤት ጎረቤት በመሆናቸው ሰምተው ከሌሎች ሰዎች ጋር ደርሰውበት ሊይዙት ችለዋል ሲሉ የ፲ አለቃ በቀለ ማሞ መናገሻ አውራጃ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ባልደረባ ገልጸዋል። (ግንቦት 29 ቀን 1960 አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ



## በግጭት ምክንያት ከቀያቸው የሚፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር ከ100 ሚሊዮን ማለፉ ተገለጸ

አዲስ አበባ፤ የተመድ የስደተኞች ኮሚሽን በግጭቶች አስገዳጅነት ከቀያቸው የሚፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር ለመጀመሪያ ጊዜ ከ100 ሚሊዮን ማለፉን አስታወቀ።

በሩሲያ እና ዩክሬን መካከል የተከሰተው ጦርነት የስደተኞችን ቁጥር ከ100 ሚሊዮን እንዲልቅ እንዳደረገው ኮሚሽኑ ማስታወቁን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል።

## ሩሲያ 963 አሜሪካውያንን እና 26 ካናዳውያንን ወደ አገሯ እንዳይገቡ አገደች

አዲስ አበባ፣ ሩሲያ 963 አሜሪካውያን እና 26 ካናዳውያን ወደ አገሯ እንዳይገቡ ማገዷን አስታወቀች።

የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ እንዳስታወቀው፥ 963 አሜሪካውያን መቼም ቢሆን ወደ አገሯ እንዳይገቡ ያገደች ሲሆን፥ እገዳው ከተጣለባቸው አሜሪካውያን መካከል በዋናነት ጆ ባይደን እና ልጃቸው ሀንተር ባይደን ይገኙበታል።

የአሜሪካ ባለሥልጣናት ፥ የአሜሪካ ሕዝብ



በሩሲያ ላይ የተዛባ አመለካከት እንዲይዝና ጥላቻ እንዲያድርበት እየሠሩ እንደሚገኙ ሚኒስቴሩ መግለጡንና ድርጊቱን መኮነኑን ታስ የተሰኘው የአገሪቷ የዜና አገልግሎት ዘግቧል።

በተመሳሳይ ወደ ሩሲያ እንዳይገቡ የታገዱት 26ቱ ካናዳውያን ፣ ሩሲያ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ድምጽ በመስጠታቸው ነው ተብሏል።

ከታገዱት ካናዳውያን መካከልም በዋናነት የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ እና ባለቤታቸው እንደሚገኙበት ነው ሽንዋ የዘገበው።

ሩሲያ የአሜሪካ ባለስልጣናትንና ሕዝብን ለይታ እንደምትመለከት፥ እንዲሁም ከየትኛውም ሃገር ጋር ግጭት እንደማትፈልግ እና በሯ ምንጊዜም ለውይይት ክፍት መሆኑን የአገሪቷ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስታወቁን ሲጂቲ ኤን ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

# ስፖርት

ማክሰኞ

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!


# ‹‹ከስህተታችን ተምረን ሕዝባችንን ለመካስ ተባብረን መሥራት ይጠበቅብናል››

**- ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን**

ቦጋለ አበበ

በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች መካከል ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት ኢትዮጵያን በ2020 ቶኪዮ ኦሊምፒክ ዋጋ አስከፍሏታል። በዚያ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ እየለመደች ከመጣችው ውጤት በተቃራኒ ዝቅተኛ የሜዳሊያ ቁጥር አስመዝግባለች። ሕዝብም በዚህ ዝቅተኛ ውጤት ቅር ከመሰኘት አልፎ ቁጣውን በተለያየ መልኩ ሲገልጽ እንደነበር አይዘነጋም። የሁለቱ ተቋማት አመራሮች ውዝግብ ለተመዘገበው ዝቅተኛ ውጤት የአንበሳውን ድርሻ ቢይዝም ከኦሊምፒኩ በኋላ ግንኙነታቸው ይበልጥ እየሻከረ መሄዱ አሳሳቢ ነበር። ሁለቱ አካላት ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው የአገርን ስፖርት ከማሳደግ ይልቅ ይባስ ብለው ከኦሊምፒኩ በኋላ በይፋ ግንኙነት ማቆማቸው ጉዳዩን ይበልጥ አሳሳቢ አድርጎት ነበር። መንግሥት በዚህ ረገድ ጣልቃ ገብቶ ሁለቱን አካላት ለመሸምገል ውዝግቡ በጦፈበት ወቅት አለሁ ቢልም ይህ ነው የሚባል ትርጉም የሚሰጥ ሥራ ሳይሠራ ቆይቷል። ይህም የፓሪሱ 2024 ኦሊምፒክ በተቃረበበት በዚህ ወቅት በቶኪዮ ኦሊምፒክ የነበረው ውዝግብ እንዳይቀጥል የብዙዎች ስጋት ነበር።

የአገሪቱን ስፖርት በበላይነት የሚመራው የመንግሥት አካል እንደአዲስ አመራሮቹ ተቀይረው ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከሆነ ወዲህ በኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መካከል የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በተለይም ካለፈው ሳምንት ወዲህ የሁለቱን ስፖርት ተቋማት አመራሮች ለማወያየትና የነበሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት መድረኮችን በማመቻቸት ያደረገው ጥረት ፍሬ ያፈራለት ይመስላል። ሁለቱ የስፖርት ተቋማት ባለፈው ዓርብ በልዩነቶቻቸው ላይ መምከራቸው የሚታወስ ሲሆን ከትናንት በስቲያም ችግሮቻቸውን ፈተው በጋራ ለመሥራት እንደተስማሙ አሳውቀዋል።



**ሁለቱ አካላት ችግሮቻቸውን ተመልክተው የመፍትሔ ባለቤት እንዲሆኑ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ለየብቻና በተናጠል መድረኮችን በማመቻቸት ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው ተገልጿል፣**

ከትናንት በስቲያ ምሽት በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋባዥነት በተዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንቶች ‹‹ካለፈው ስህተታችን ተምረን ሕዝባችንን ለመካስ ተባብረን መሥራት ይጠበቅብናል›› በማለት የጋራ መግባባት ላይ መድረሳቸውን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ እና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በመድረኩ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ለየብቻ እና በተናጠል መድረኮችን በማመቻቸት ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲመለከቱትና የመ ባለቤት እንዲሆኑ ያደረጉበት የአመራር ብስለታቸውን በማድነቅ አመስግነዋል።

ሚኒስትሩ በበኩላቸው ‹‹ችግ ሮች ወዲያው ካልተፈቱ መዘዛቸው ዋጋ ያስከፍላል›› በማለት ከቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ውጤት መቀነስ ጋር ተያይዞ ከዝግጅት እስከ ፍጻሜ የነበረውን ሁኔታ አስመልክቶ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና ከኢትዮጵያ አትሌትክስ ፌደሬሽን ጋር የተናጠል እና የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት በተፈጠሩ ችግሮች ላይ መግባባት ላይ መደረሱን ገልፀዋል።

ሚኒስትሩ ችግሮቹ ቀላል እንደነበሩ እና ቶሎ ባለመፈታታቸው እንዲደራረቡ እና እንዲባባሱ በመደረጋቸው ዋጋ ወደ ማስከፈል ተሸጋግረው ለመንግሥትም ትልቅ የቤት ሥራ ሆነው እንደነበር በማስታወስ ‹‹ችግሮች እንዳይከሰቱ በመከላከል እና ከተከሰቱም ቶሎ ለመፍታት መሥራት ያስፈልጋል›› ብለዋል።

የተከሰቱት ችግሮች መነሻቸው ከየት እንደሆነ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በጥልቀት የገመገመ ሲሆን በዋናነት ሁለቱ አካላት ከተሰጣቸው ኃላፊነት አኳያ ሕግና አሠራርን ተከትለው ሳይናበቡ በመሥራት የተፈጠሩ እንደነበሩ አቶ ቀጄላ ተናግረዋል። በዚህ መሠረት ሁለቱ አካላት የተሠጣቸውን ኃላፊነት ተናበው እና ተስማምተው የሚሠሩ ከሆነ ችግሮች እንደማይፈጠሩ ያላቸውን ተስፋ ገልፀዋል። ችግሮች ከዚህ በኋላ ከተፈጠሩም በአስቸኳይ መፍትሔ እየተሰጣቸው በመሄድ ጤናማ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ሁሉም የበኩሉን ሚና መወጣት እንዳለበት ሚኒስትሩ አሳስበዋል።

የሁለቱ ስፖርት ተቋማት አመራሮች ከዚህ ቀደም ከአንዴም ሁለቴ በተለያዩ ጉዳዮች አለመግባባት እየፈጠሩ ሲወዛገቡ የነበረ ሲሆን ታርቀናል ወይም ልዩነቶቻችንን ተነጋግረን ፈተናል ካሉ በኋላ ዳግም ሲቃቃሩ እንደነበር ይታወሳል። በተለይም ኦሊምፒክን የመሳሰሉ ታላላቅ የውድድር መድረኮች በተቃረቡ ወቅት በአትሌቶች ምርጫ እንዲሁም ከዝግጅት ጋር በተያያዘ በጉዳዩ ላይ ‹‹እኔ ነኝ አዛዥ›› በሚል ሲካረሩ ማየት የተለመደ ነው። አሁንም ሁለቱ አካላት ‹‹ከስህተታችን ተምረን በጋራ እንሠራለን›› ብለው ቃል ቢገቡም ከአትሌቶች ምርጫና ዝግጅት ጋር በተያያዘ ነገም ተመሳሳይ አለመግባባት ውስጥ እንዳይገቡ በርካቶች ስጋት አላቸው። አሁን በምን ጉዳይ ላይ እንደተግባቡ የተገለፀ ነገር አለመኖሩም ነገ በተመሳሳይ ውዝግብ እንዳይጠመዱ ስጋት ነው። ለዚህም ከዚህ ቀደም አወዛጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ለሁሉም ግልፅ የሆነ ሕግና ሥርዓት ማበጀትና በዚያም መሠረት መመራት እንደሚያስፈልግ የስፖርት ቤተሰቡ እምነት ነው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የብዙዎችን ሕይወት የቀየረው የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር

በዓለምነህ ቸርነት

ጊሳ በአማራ ክልል አዊ ዞን ዳንግላ ወረዳ በ1973 ዓ.ም የተቆረቆረች የገጠር ከተማ ነች። ከዳንግላ ከተማ በ31 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ይህች የገጠር መንደር መብራት እንኳን ያገኘችው በ1999 ዓ.ም ነው። ነገር ግን ከተማዋ አሁን በፈጣን እድገት ላይ ትገኛለች። በገጠር መንደሯ በ2003 ዓ.ም የተመሠረተውና የሶሰር አባል የሆነው መድኃኔዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር ለዚህች የገጠር ከተማ እድገት ትልቁን አስተዋጽኦ አበርክቷል።

መድኃኔዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር በአካባቢው በንግድ ሥራ ለተሠማሩ አባላቱ እያስቆጠበ ብዙ ሚሊዮን ብር ብድር በመስጠት ትርፋማ ነጋዴዎችን በማብዛት ሕይወታቸው እንዲቀየር አድርጓል። በዚህም በርካቶች የተሻሉ ቤቶችን በአካባቢው እንዲሠሩ አስችሏቸዋል። ከዚህ በፊት የሌሎች ሰዎች ተሸከርካሪዎች ሲያልፍና ሲያገድም እንደ ብርቅ ነገር ሲመለከቱ የነበሩት አባላት አሁን እራሳቸው በብዛት መኪኖችን በእጃቸው አስገብተዋል። ይህ ተግባራቸው ታዲያ በመንግሥት አስተዳደር ላይ ጫና ፈጥሮ ወደ መንደሯ የሚያስገባ ጥርጊያ መንገድ እንዲሠራ ምክንያት ሆኗል።

ማኅበሩ ነጋዴው ብቻ እየቆጠበ እንዲለወጥ የሚያደርግ አይደለም። ይልቁንም በከተማዋ የሚገኙ የደሃ ደሃ በተለይም ለሴቶች ያለወለድ ጭምር ብድር በመስጠት እየሠሩ እንዲለወጡ እድል ፈጥሯል። ከእነዚህ መካከል በቡና ንግድ ተሰማርታ ዛሬ ባለ መኪና ለመሆን የበቃችው እንስት እንደምሳሌ የምትጠቀስ ነች።

11 ቅጥር ባለሙያዎች ያለው መድኃኔዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማሕበር 8 ሚሊዮን የዕጣ ካፒታል ያለው ሲሆን ከቁጠባ ጋር አጠቃላይ ካፒታሉን ወደ 33 ሚሊዮን ብር አድርሷል። ማኅበሩ ኮምፒተራይዝድ የሆነ ሲስተም በመጠቀም አሠራሩን ያዘመነ ነው። ሲስተሙ ከሶሰር ዩኒየኑ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ የተቀላጠፈ የፋይናንስ ትስስር እንዲኖር አስችሎታል።

ማኅበሩ ከዝቅተኛ ቁጠባ 10 ብር ጀምሮ ያስቆጥባል። ይሄም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታስቦ ነው። የብድር ጣሪያው ከዚህ በፊት 1.5 ሚሊዮን ብር ነበር። አሁን በሃገራችን ካለው ግሽበት አንጻር 2 ሚሊዮን ብር ደርሷል። ማኅበሩ የሶሰር አባል በመሆኑ አባላት የቆጠቡትን በስድስት እጥፍ የጠለፉ ዋስትና አሲዘው ቤት ካላቸው፤ ቤታቸውን ማስያዣ በማድረግ ከዩኒየኑ ብድር እንዲወስዱ ያደርጋል። ማኅበሩ እስከ አሁን ካሰራጨው ከ63 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር ውስጥ 16 ሚሊዮኑ ከዩኒየኑ የተገኘ ነው። የብድር አመላለሱም በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል።

አቶ ስለሺ ከፍያለ የዚህች የገጠር መንደር ነዋሪና የማኅበሩ አባል ናቸው። ማኅበሩ በ2003 ዓ.ም ከተቋቋመ ጀምሮ እየቆጠቡ በተሻለ ሁኔታ የብድር ተጠቃሚ ሆነዋል። አቶ ስለሺ በራሳቸው 1 ሺ ብር መደበኛ ቁጠባና 1 ሺ ብር ደግሞ ዕጣ ይከፍላሉ። በባለቤታቸውና በልጃቸው እንደዚሁ 1 ሺ ብር ቁጠባና 1 ሺ ብር ደግሞ ዕጣ አላቸው።

አቶ ስለሺ ሁኔታው እንዲህ ያስረዳሉ "ከመድኃኔዓለም በባለቤቴ 1 ሚሊዮን ብር በኔ እስከ 635 ሺ ብር ብድር ወስጄ ወፍጮዎችን ተክዬ እየሠራሁኝ ነው። ከኔ ጋራ 6 ሠራተኞች አሉ። ከዚህ ሌላ የጣውላ ማሽን ሥራ ከፍቼ እስከ ፊኒሺንግ ሥራ ቢያንስ ለ 5 ሰዎች የሥራ እድል ፈጥሬያለሁ። በ2010 ዓ.ም ደግሞ ጥሩ ተሽከርካሪ ገዝቼ እየተጠቀምኩ ነው። ለሹፌርና እረዳት የሥራ እድል ፈጥሬያለሁ" የሚሉት አቶ ስለሺ እነዚህን ሁሉ ሥራዎች እንዲሠሩ ትልቁን አስተዋጽኦ ያበረከተላቸው መድኃኔዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር መሆኑን ይመሰክራሉ። አሁን የራሳቸውን የቁጠባ መጠን 250 ሺ ብር፣ የባለቤታቸውን ከ300 ሺ ብር በላይ እና የልጃቸውን ደግሞ 100 ሺ ያደረሱት አቶ ስለሺ በየወሩ ብድራቸውን እየመለሱ በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።

አቶ ታጀበ አየነው በዚህው የገጠር ከተማ በ01 ቀበሌ የሚኖሩ ነጋዴ ናቸው። በ2003 ዓ.ም ከምሥረታ ጀምሮ አባል የሆኑት አቶ ታጀበ ምንም ሳይኖራቸው አስር ሺ ብር ተበድረው መቆጠብ እንደጀመሩ ይናገራሉ። ሁኔታውን እንዲህ ያስረዳሉ"በመጀመሪያ በ2004 ዓ.ም 60 ሺ ብር ስበደር ዋስ የሆነኝ ጓደኛዬ ነበር። ያንን መለስኩ በሁለተኛው ዙር እንደዚሁ 90 ሺ ብር ተበድሬ ያንንም መለስኩ። ከዚያ በኋላ 400 ሺ ብር ተበድሬ ቤት ሠርቼ እንደገና 900 ሺ ብር ብድር ወሰድኩኝ። ያንንም መልሼ ከባለቤቴ ጋር 1.8 ሚሊዮን ድረስ ተበድሬ ተሳቢ መኪና ገዛሁኝ። 1 ዓመት ተጠቀምኩበት። ተሳቢ መኪናው ድምበር ተሻጋሪ በመሆኑ በሰላም መደፍረስ ምክንያት ስጋት ሲገባኝ ሸጥኩት። አሁን ሶስት ቤቶች እና አጠቃላይ ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል አለኝ፤ በጥሩ ደረጃ ላይ ነው ያለሁት" ሲሉ ይገልጻሉ።

መድኃኒዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማኅበርን እንደምሳሌ ወሰድን እንጂ የዩኒየኑ አባል የሆኑ ሌሎች በርካታ አባል መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተመሳሳይ የእድገት ጎዳና ላይ ናቸው። አንድ ዩኒየን ማደግ የሚችለው አባላቱን አብሮ ሲያሳድግ መሆኑን ከሦሰር የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዩኒየን መማር ይቻላል። መድኃኔዓለም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ዩኒየኑ ብድር ከመስጠት ሌላ ስልጠና፣ የቴክኒካል እገዛና የኦዲት አገልግሎት በመስጠት አግዟል። ማኅበሩ አቅሙን አጎልብቶ አሁን ላይ የራሱን ሥራ አስኪያጅ እስከሚቀጥር ድረስ ዩኒየኑ ማናጀር ቀጥሮ ሲደግፍ ቆይቷል። ሲስተሙን ኮምፒተራይዝድ ከማድረግ አንጻር በርካታ ድጋፍ አድርጓል። አስፈላጊ የቁሳቁስ ድጋፍ ሰጥቷል። ዩኒየኑ ለማኅበሩ በጣም ቅርብ ነው ማለት ይቻላል።

መድኃኔዓለም በዚህች የገጠር መንደር በሰለጠነ ባለሙያና በተሻለ ቴክኖሎጂ እየሠራ ያለ የፋይናንስ ተቋም ሆኗል ። ያለው ካፒታልና ያሰራጨው ብድር በጣም ጥሩ የሚባል ነው። በሚሊዮን ደረጃ ተበድረው ያንን ኢንቨስት አድርገው በአግባቡ የሚመልሱ አባላት አሉት። ቀደም ሲል መኪና አልፎ ሲሄድ ነበር የሚያዩት አሁን ግን እነዚህ አባላት መኪናውን እራሳቸው ለመያዝ በቅተዋል። ለነጋዴዎች ብቻ የቆመ ባለመሆኑ ለደሃ ሴቶችም ያለምንም ወለድ ብድር በማሰራጨት ሕይወታቸውን ቀይሯል። ይሄ ዩኒየን እንጂ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር አይመስልም ብንል ማጋነን አይሆንም።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ